www.abyssinialaw.com

11ኛ አመት ቁጥር 11 11th Year No 11	ባህር ዳር መስከረም 4 ቀን 1998 ዓ.ም Bahir Dar 14th Septeber2005

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ-ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATICE REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 7.90 Price	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 37/1998 ዓ.ም. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	Regulation No. 37/2005 Amhara National Regional State City Administrations and Municipalities Finance Administration, Council of Regional Government Regulation.

ደንብ ቁጥር 37/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

የአካባቢ የራስ በራስ አስተዳደርን ለመረከብ ብቁ የሆኑ የክልሉ ከተሞች መልካም አስተዳደርን በማስፈን ነዋሪው ሕዝብ ቀጥተኛ ተሣታፊ ሊሆን የሚችልበትን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሊገነባና የፈጣን ልማት ተጠቃሚ ለመሆን ይቻለው ዘንድ ምቹ፣ ግልፅ ፍትሐዊ፣

REGULATION NO. 37/2005

A REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE FINANCE ADMINISTRATION OF CITY ADMINISTRATIONS AND MUNICIPALITIES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

Whereas, it has been found appropriate to enable those cities of the Region qualified to take over local self government to have favorable, transparent, just, efficient and effective finance administration framework so that they

www.abyssinialaw.com

የተሟለጠና ብቁ የፋይናንስ አስተዳደር ማዕቀፍ እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

could put in place good governance and a democratic system in which the resident public directly participate and be beneficiary of accelerated development thereof;

የተሟላ የአካባቢ አስተዳደር ስልጣን ለመረከብ ያልበቁ ማዘጋጃ ቤቶችና ታዳጊ ከተሞች ደግሞ በህግ የተሰጧቸውን ተግባርና ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚያበቃቸውን ተገቢ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መቅረፅ ተገቢ እንደሆነ በመታመኑ፣

Whereas, it has, on the other hand, been found appropriate to design and implement appropriate finance administrative system which may enable those municipalities and emerging cities that are not capable of taking over full local self-government in order to carryout the responsibilities they are legally bestowed upon;

የብሔራዊ ክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በተሻሻለው የክልሉ ከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል::

Now, therefore, Council of the Amhara National Regional Government, inaccordance with the powers vested in it under the provisions of art. 58, sub art 7 of the revised Regional Constitution and art. 50, sub art 3 of the revised Regional State Cities' Establishment, Organization and Definition of their Powers and Duties Proclamation No. 91/2003, as amended, thereby issues this regulation:

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

PART ONE
GENERAL

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 37/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

1. Short Title

This regulation may be cited as "City Administrations and Municipalities Finance Administration, Council of the Regional Government regulation No. 37/2005."

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

1. "አዋጅ" ማለት የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ ነው::
2. "ማዘጋጃ ቤት" ማለት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን ለመስጠት የተቋቋመና በራሱ ስራ አስኪያጅ የሚመራ የአገልግሎት ዘርፍ ነው::
3. "በገቢ ክፍፍል ስርዓት መሠረት የተገኘ ገቢ" ማለት ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወጣ የገቢ ክፍፍል

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

1. "Proclamation" means the revised Amhara National Regional State Cities Establishment, Organization and Determination of Powers and Duties Proclamation No. 91/2003, as amended.
2. "Municipality" means a service sector established to render municipality services and managed by its own manager.
3. "Revenue obtained as per revenue sharing system" means a fund which is transferred from the Regional State to city administrations on the bases

www.abyssinialaw.com

ቀመር ተደግፎ በክልሉ መንግስት ወደ ከተማ አስተዳደሮች የሚተላለፍ ገንዘብ ነው::

4. "የካፒታል ፕሮጀክት" ማለት የሕዝብ አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ ተጨማሪ የመሰረተ ልማት አውታሮችን ወይም የእነዚህኑ ማሻሻያዎች መገንባት፣ ቋሚነት ያለው ንብረት ማፍራት፣ መሣሪያዎችን መግዛት ወይም አንድን ተቋም ወይም አካባቢ በአስፈላጊ መሣሪያዎች ማደራጀት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል:-

ሀ. ከፍ ብሎ ለተመለከቱት ስራዎች ክንውን ለተካሄዱ ጥናቶች ምርምሮችና ለተነደፉ የመጀመሪያ ደረጃ ዕቅዶች የተደረጉ ወጪዎች፣

ለ. የግንባታ ሥራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ ለባለሙያ መረጣ፣ ለሙያ አገልግሎት ክፍያ፣ ለህትመት ወይም ለቀረፃ፣ ሰነዶች ዝግጅትና የማባዛት ስራ፣ ለማስታወቂያዎች አወጣጥ፣ የባለቤትነት መብትን ለማግኘት፣ የቦንድ፣ የመድን እና የወለድ ወጪዎችን ጨምሮ፣ ከእነዚህ ተጨማሪ ግንባታዎች ወይም ማሻሻያዎች፣ ንብረት የማፍራት ወይም ከግዥ ተግባራት ጋር በተያያዘ የተፈፀሙት ተጓዳኝ ወጪዎች፣

ሐ. ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩት ወጪዎች ከፍያ የዋለን ገንዘብ ለመተካት የወጣ ወጪ፣

መ. የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት የተደረገ ወጪ፣

5. "የከተማ አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤት ገቢ" ማለት ከከተማ ነክ አገልግሎቶች ወይም ከማዘጋጃ ቤት ታክሶች፣ የዕቃና አገልግሎት ክፍያዎች፣ የተለያዩ ገቢዎች፣ ከክልሉ መንግሥት ጋር በክፍፍል የተገኙ ገቢዎች፣ የክልሉ መንግሥት ድጐማ ዕርዳታዎች እና ሌሎች የፋይናንስ ድጋፎች፣ የቦንድ ሽያጭ፣ ለከተማው ከተሰጡ የተስፋ ሰነዶች እና የወጪ መጋራትን መሠረት በማድረግ ከማናቸውም ሌሎች ከከተማው ጋር ከተገቡ ግዴታዎችና ከብድር ስምምነቶች የሚገኝ ማናቸውም ገንዘብ ነው::

of revenue sharing formula to be issued from time to time.

4. "Capital project" means constructing additional infrastructures or betterment thereof, aquiring fixed asset, procuring machines or equipping an institute or a locality with necessary instruments with the view to rendering public service, including the following:

A. expenditures spent for the accomplishment of studies, researches as well as drafted preliminary plans so as to effectuate the duties cited hereinabove;

B. expenditures spent, during the construction works, for the purpose of selection of professionals; for professional service charge, and publication, mulding, document preparation and duplicating activities, advertisements, patent,including bond, premium and interest expenditurers, or parallel expenditure executed in relation to these procurement activities, additional or improving construction works or aquision of property;

C. expenditures used to recover the fund spent for the payment of the expenditures state hereinabove;

D. expenditure spent to launch a working procedure;

5. "City administration or municipality revenue" means any form of money to be obtained from urban services or municipal taxes, goods and service charges, various revenues, revenues obtained from sharing system with the Regional government, subsidy from the Regional State and other financial supports; sale of bond, promisery note rendered to the city as well as any kind of fund to be obtained from any other commitment made with the city on the bases of cost sharing and from loan agreements.

www.abyssinialaw.com

6. "ሀብት" ማለት ከተለያዩ ምንጮች የተገኘ ገቢ፣ ቀሪ ሂሣብ፣ የልማት ድርጅቶች ገንዘብ ወይም ሌላ ተዘዋዋሪ ሂሣብ እና ከሌሎች ምንጮች የተገኘ ማናቸውም ገንዘብ ወይም ንብረት ነው::
7. "የልማት ድርጅት ገንዘብ" ማለት በከተማ አስተዳደሩም ወይም በማዘጋጃ ቤቱ ስር ተደራጅተው አገልግሎት የሚሰጡ የልማት ድርጅቶች የሚያፈሩት ገንዘብ ነው::
8. "የበጀት ስልጣን" ማለት በተሰበሰበ ወይም ይሰበሰባል ተብሎ በሚገመት ወይም በሚጠበቅ ሀብት የሚሸፈን፣ የካፒታል ወጪን ጨምሮ በከተማ አስተዳደር ልዩልዩ የሥራ ክፍሎችና ድርጅቶች ለሚከናወን የሥራ እንቅስቃሴ እንዲፈቀድ የተጠየቀ ወይም ወጪ ለማድረግ የተሰጠ ሥልጣን ነው::
9. "የጋራ የፋይናንስ ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በከተማ አስተዳደሮችና በክልል መንግሥት በጋራ የተቋቋመና በደንቡ የተሰጡትን ተግባራት ሁሉ የሚያከናውን ቦርድ ነው::
10. "የመነሻ ሂሣብ ግምት" ማለት የከተማ አስተዳደር እና የክልል መንግሥት የጋራ የፋይናንስ ቦርድ ለሚሰጠው ውሣኔ መሰረት በመሆን የሚያገለግልና በክልሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ተወስኖ ለከተማ አስተዳደሮች የሚከፋፈል ጠቅላላ ሂሣብ ነው::
11. "የገንዘብ ድጋፍ" ማለት በጋራ የፋይናንስ ቦርድ አማካኝነት በየጊዜው እየተዘጋጀ በክልል ምክር ቤት በሚፀድቅ ቀመር መሠረት የሚከፋፈልና የክልሉ መንግሥት በጥቅል ወይም በተለየ ዓላማ ለከተማ አስተዳደሮች የሚመደብ ገንዘብ ነው::
12. "የተጠቃለለ ፈንድ" ማለት በአንድ የከተማ አስተዳደር ወይም ለዚሁ ጉዳይ ኃላፊነት በተሰጠው የሥራ ክፍል ስም በባንክ ሂሣብ ያለ ወይም በካዝና የተቀመጠ ገንዘብ ነው::
13. "ድሐ" ማለት ከተወሰነው የድህነት ወለል በታች የሆነ እና የመክፈል አቅም የሌለው መሆኑ አግባብ ባለው የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት በኩል የተመሰከረለት ሰው

6. “Assets” means revenue from various sources, ending balance, fund of development enterprises or other current account as well as any other fund or property obtained from other sources.
7. “Fund of development enterprise” means fund acquired by development enterprises that are organized under the city administration or the municipality so as to render service.
8. ”Budget authority” means an authority vested to appropriate or withdraw the resource collected or expected to be collected, incliding capital expenditures for activities to be accomplished by various work units and organizations of the city administration.
9. ”Common financial board” means a board jointly established by city administration and the Regional state pursuant to this regulation and accomplish all duties given to it
10. ”Assessment of initial capital” means a consolidated fund which serves as the basis for the decision to be made by the common financial board of city administration and the Regional state and be apportioned to city administrations upon the determination of the Regional Finance and Economic Development Bureau head.
11. ”Financial assistance” means the fund which is prepared occasionally by the common financial board, apportioned pursuant to the formula approved by the Regional Council and allotted to city administrations by the Regional state either in total or for special purpose.
12. ”Consolidated fund” means money put in a bank account in the name of a city administration or a work division which is made responsible for this purpose, or that is put in a coffer.
13. ”Poor” means a person who is below the determined poverty line and authenticity hereof ratified by the relevant city or woreda administrative council as having no capacity to pay.

www.abyssinialaw.com

ነው::

14. "መሠረታዊ አገልግሎት" ማለት መሠረታዊ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶችን እንዲሁም አግባብ ባለው የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር ም/ቤት "መሠረታዊ አገልግሎቶች" ናቸው ተብለው በተጨማሪ የተሰየሙ ሌሎች አገልግሎቶችን ይጨምራል::

15. "ቢሮ" ማለት የአብክመ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ነው::

14."Basic Service" includes basic health and education services as well as other service additionally designated as the " basic services" by the relevant city and woreda administrative councils.

15."Bureau" means the Amhara National Regional State Works and Urban Development Bureau.

3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ ደንብ በከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች ፋይናንስና ንብረት ነክ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም ታዳጊ ከተሞች ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ በሚወጣ መመሪያ እየሰሩ ሊቆዩ ይችላሉ::

3. Scope of Application

1. This regulation shall apply to financial and property related affairs of city administrations and municipalities.
2. Notwithstanding the provision stipulated under sub art 1 of this article, emerging cities may stay working by a directive to be issued cross-checked against the provisions of this regulation.

4. ዓላማዎች

ደንቡ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል:-

1. የከተሞችን ቋሚ የፋይናንስና የሀብት አስተዳደር ስርዓት መመስረትና በስራ ላይ የሚውሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
2. ገንዘብ ሊሰጠው የሚችለውን ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘትና ይኸው አፈፃፀም የሚጠይቀውን ብቃትና ውጤታማነት ማረጋገጥ::

4. Objectives

The regulation shall have the following objectives:

1. to establish permanent financial and resource administration systems of the cities and to create conducive situation for their implementation;
2. to cause the acquisition of equivalent value that money may render, and ensure the efficiency and effectiveness of the implementation thereof.

ክፍል ሁለት
ስለገቢ

PART TWO
REVENUE

5. የገቢ ምንጮች

የከተማ አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤት ገቢ ከሚከተሉት የሚመነጭ ይሆናል:-

1. ከከተማ ወይም ማዘጋጃ ቤት ነክ አገልግሎቶች የሚሰበሰብ ገቢ፣
2. ከክልሉ መንግስት ጋር በሚደረግ የገቢ ክፍፍል ስርዓት ተወስኖ የሚገኝ ድርሻ፣
3. ከክልሉ መንግሥት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከተው ወረዳ አስተዳደር በኩል የሚሰጥ ድጐማ፣

5. Sources of Revenue

The revenue of city administration or municipality may arise from the following:

1. revenue to be collected from city or municipal services:
2. share to be obtained upon the determination of revenue sharing system with the Regional State;
3. subsidy granted by the Regional State or, as deemed necessary, from the concerned woreda administration;

www.abyssinialaw.com

4. ለተለየ ተግባር ማስፈፀሚያ እንዲውል ከክልሉ መንግስት የሚሰጥ የበጀት ድጋፍ፣
5. ብድር፣
6. መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚገኝ የአይነትም ሆነ የጥሬ ገንዘብ እርዳታ፣
7. ሌሎች፡፡

6. ስለከተማ አገልግሎት ወይም ማዘጋጃ ቤት ነክ ገቢዎች

በዚህ ደንብ መሠረት የከተማ አገልግሎት ወይም የማዘጋጃ ቤት ገቢዎች የሚባሉት ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው:-

1. በማዘጋጃ ቤቶች የገቢ ታሪፍ ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 12/1992 እና አዲስ በተደራጁ ማዘጋጃ ቤቶች የገቢ ታሪፍ መወሰኛ ደንብ ቁጥር 20/1996 ዓ.ም. ድንጋጌዎች ስር የተዘረዘሩ ገቢዎች፣
2. በሽግግር ወቅት እንዲቆዩ የተወሰነላቸውን ነበር የከተማ ቦታ ይዞታዎችና ከሊዝ ስርዓት ውጭ የከተማ ቦታዎችን ለማስተዳደርና የኪራይ ተመናቸውን ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር 1/1987 ዓ.ም. እና የከተማ ቦታን በሊዝ ይዞታ ለማስተዳደር በወጣው ደንብ ቁጥር 2/1987 ዓ.ም. /እንደተሻሻሉ/ እና በነባር የከተማ ቦታ ይዞታዎች ማጣሪያ መስፈርቶችና የኪራይ ተመን መወሰኛ መመሪያ ቁጥር 11/1996 ዓ.ም. ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰበሰብ የከተማ ቦታ ኪራይና የሊዝ ገቢ፣
3. በሌሎች የከተማ ቦታ አጠቃቀም መመሪያዎች መሠረት የሚጠየቅና የሚሰበሰብ ክፍያ፣
4. በማናቸውም የከተማ አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤት ከተማ ስር ከሚተዳደሩ የልማት ድርጅቶች በዲቪደንድ መልክ የሚሰበሰብ ገቢ፣

7. በከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች ግብር ስለሚወሰንበት ሁኔታ

1. የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች የንብረት ግብርን በሚወስኑበት ጊዜ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ታሣቢዎች መሠረት ማድረግ ይኖርባቸዋል:-

4. budget subsidy to be granted by the Regional State for the implementation of special purpose;
5. loan;
6. aid to be obtained from governmental and non-governmental organizations either in kind or in cash;
7. other sources.

6. City Service or Municipal Revenues

The following are, pursuant to this regulation, said to be city service or municipality revenues:

1. Revenues listed under the provisions of Municipalities Revenue Tariff Amendment Regulation No.12/2000 as well as Newly Organized Municipalities Revenue Tariff Determination Regulation No.20/2004,
2. City land rental fee and lease revenue to be collected pursuant to formerly held urban lands and lands in lease exempted towns designated to stay under transitional period regulation No.1/1995 and the administration of urban lands under lease holding regulation No.2/1995, as amended, as well as former urban land holding screening criteria and fee rate determination directive No.11/2004,
3. Payment to be requested and collected pursuant to other urban land use directives;
4. Revenue to be collected as a dividend of development enterprises administrated under any city administration or municipal city.

7. Condition of Determining Tax by City Administration and Municipalities

1. City administrations and municipalities shall consider the assumptions listed below where they asses property tax:

www.abyssinialaw.com

ሀ. ንብረቱ ለሚገኝበት የከተማ ቦታ በተሰጠው ደረጃ መሠረት የተወሰነው ተመን ወይም የመሬቱ ዋጋ ግምት፤

ለ. ለመሬቱ እና በላዩ ላይ ላረፈበት ሕንፃ በጣምራ የተወሰነው ተመን፤

ሐ. ቀደም ሲል ተመናቸው ላልተወሰነ አካባቢዎች አንድ አይነት ተመን በሥራ ላይ የዋለ ሆኖ ሲገኝ ዋጋቸው ከግምት ውስጥ ሣይገባ ደረጃቸው የሚወሰንበት የተመን አሰጣጥ ሥርዓት፤

2. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ዘዴዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ፤

ሀ. ለመሬት ዋጋ አተማመን መሠረቱ የመሬት የሊዝ ዋጋ፣

ለ. ለሕንፃ ዋጋ አተማመን መሠረቱ የአካባቢው የኪራይ ዋጋ፣ ይሆናል::

3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩት ሌሎች የገቢዎች ምጣኔ በሚወሰንበት ጊዜ አግባብ ያለው ከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት የሚጠይቀው አጠቃላይ ወጪ ከነዋሪው ሕዝብ ብዛት አንፃር፣ በፌዴራል እና በክልል መንግስታት የሚጣሉና የሚሰበሰቡ ሌሎች ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያለሆኑ ታክሶች ድምር ውጤት የሚያስከትለው ጥቅል ጫና ግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል:: ይህንኑ በሚመለከት የሚኖረው አሠራር ደንቡን ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

A. assessed rate or estimated land value as per the class of urban cite where the property is found;

B. rate determined for both the land and building erected on it:

C. rating system that determines their grade without taking values into account where uniform of rate is found functional for those areas whose rate was not determined previously,

2. Where the above methods are put into effect the following are taken into account:

A. land lease value as a basis of rating of land rent value;

B. local rent value as the basis for rating of value of building.

3. Where the rate of revenues listed under art. 6 of this regulation is assessed, the total expenditure which the relevant city administration or municipality service may request shall take into account the number of residents as well as the total burden caused by the total effect of direct and indirect taxes imposed by the federal and regional governments. The working procedure coming into forth concerning this shall be determined by a directive to be issued following the regulation.

8. ስለዕቃና አገልግሎት ክፍያዎች አወሣሰን

1. ሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን ምጣኔ በሚወሰንበት ጊዜ የሚከተሉትን መርሆዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል:-

ሀ. በግብር ከፋዩ ኅብረተሰብ ዘንድ ፍትሃዊ ሆኖ ለመገኘት እንዲቻል ለሚያቀርበው አገልግሎት የሚያስፈልገው የወጪ ጫና በአጠቃላዩ የግብር ከፋይ ኅብረተሰብ ላይ ከሚያርፍ ይልቅ የአገልግሎቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ በሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ

8. Assessment of Property and Service Charges

1. Without prejudice to the provision of other laws, any city administration or municipality shall take the following principles into account where it assesses the rate of fees and charges:

A. The promotion of fairness in the eyes of tax payers by shifting the costs of a particular activity from tax payers at large to the specific users who benfit most directly from that activity;

www.abyssinialaw.com

የሚያርፍበትን መንገድ መፈለግ፣

ለ. የዕቃዎችና የአገልግሎቶች አቅርቦት እና ፍላጐት የገበያ ሥርዓትን እንዲከተል በማድረግ የሀብት አጠቃቀም ብቃትን ማሣደግ::

2. የክፍያ ምጣኔው ሲወሰን የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙት የህብረተሰብ ክፍሎች በስተቀር ማናቸውም ቤተሰብ ለሚጠቀምበት አገልግሎት የሚያስፈልገውን ሙሉ ወጪ መሸፈን ያለበት መሆኑን፣

ለ. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወገኖች ቢያንስ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ይችሉ ዘንድ የድጐማ ስርዓት ተጠቃሚዎች መሆናቸውን፣

ሐ. የክፍያ አወሳሰን ፖሊሲው ለሁሉም የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ግልፅ መደረጉን፣ እና የተሰጡ ድጐማዎችም ሆኑ የተደረጉ አስተያየቶች ሁሉም ተጠቃሚዎች ማወቅ በሚችሉበት አኳኋን ሥራ ላይ መዋላቸውን፣

መ. የክፍያው አወሣሰን ሥርዓት የሚያስከትለው ድምር ውጤት በንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና ያለማስከተሉን፣

ሠ. የከተማውን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሠረት በማድረግ የታሪፍ ሥርዓቱ በየጊዜው ማስተካከያ የተደረገበት መሆኑን፣

ረ. የክፍያ ግዴታቸውን የማይወጡ ወገኖች ላይ አስተማማኝ የሆነ የማስገደጃ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓትና የማስፈፀሚያ ስልት የተዘረጋ መሆኑን::

9. ስለማፅደቅ

የከተማው አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን እና በነባር ክፍያዎች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ማናቸውንም ለውጥ በሚመለከት መጠናቸው በድርድር በገበያ ዋጋ በከተማ አስተዳደሩ ወይም ማዘጋጃ ቤቱና በሌላ

B. The promotion of a more efficient allocation of resources by introducing a commercial type discipline on the demand for and supply of goods and services.

2. Where the rate of pay is assessedd, it shall take the following into account:

A. That any family with the exception of those who are leading a low standard of living shall cover the full expense necessary for the service it receives;

B. Whether those people who lead low standard of living are beneficiaries of a subsidy system at least to fulfill the basic services;

C. Whether the payment assessment policy is made transparent to all beneficiaries as well as the provided subsidies and recommendations are effectuated in a manner that the beneficiaries may be aware of;

D. That the total effect caused by the payment assessment system doesnot bring about unnecessary burden upon business activities;

E. That amendement is made on the tariff system from time to time in line with the economic development of the city;

F. That reliable system enabling to take forceable major on those people who are unable to meet their payment obligations and impelemenation strategy is launched.

9. Approval

Unless determined by negotiation, market value or by any other organ in accordance with the law of the city administration, municipality or other relevant law, the city administrations or the municipalities shall submit the decisions arrived at by the city council or relevant

www.abyssinialaw.com

አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በሌላ አካል የሚወሰን ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በከተማው ም/ቤት ወይም አግባብ ባለው ወረዳ አስተዳደር ም/ቤት የተደረሰበትን ውሣኔ ከአስተያየት ጋር ይፀድቅለት ዘንድ ለቢሮው ያቀርባል:: ቢሮውም ይህንኑ ውሣኔና አስተያየት በማጠናቀርና በመገምገም አጥንቶ ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አቅርቦ ያፀድቃል::

10. ስለገቢ አሰባሰብ

1. ማንኛውም የከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት በዚህ ደንብ መሰረት ግብር፣ታክስ፣የዕቃና አገልግሎት ክፍያ ወይም ሌሎች ገቢዎችን የሚወስን፣ የሚሰበስብና የሚመዘግብ የራሱ የሆነ አደረጃጀት ይኖረዋል::
2. የከተማ አስተዳደሩ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም በማዘጋጃ ቤት ደረጃ በወረዳ የሚገኝ መሪ ማዘጋጃ ቤት ማንኛቸውም ገቢ የሚወሰንበትንና የሚሰበሰብበትን ደረሰኝ ያሣትማል፣ እንዲሠራጭም ያደርጋል:: ስለዝርዝር አሠራሩ ቢሮው መመሪያ ያወጣል::
3. በከተማው አስተዳደር ወይም በማዘጋጃ ቤቱ ደረሰኝ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ገቢ ታክስ ወይም የዕቃና አገልግሎት ክፍያ መሰብሰብ አይቻልም::

11. ስለማስታወቅ

1. ማንኛውም የንብረት ባለቤት ወይም የከተማው አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ወይም በዚህ ደንብ መሰረት ግብር፣ታክስ ወይም የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ የመፈፀም ግዴታ ያለበት ሰው ለዚሁ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አስታውቆ መክፈል አለበት::
2. የሚፈለግበትን ግብር ወይም የዕቃና አገልግሎት ክፍያ አስታውቆ ያልከፈለ ማናቸውም ሰው አግባብ ያለው አካል በሚወስነው መሰረት በዚህ ደንብ ከተጣለበት ቅጣት ጋር ፍሬ ግብሩን እንዲከፍል ይደረጋል::

12. ስለግብር አወሣሰን

1. በከተማ አስተዳደር የከተማ ምክር ቤት

woreda administrative council with regard to the rate of fees, charges and any charges necessary to be made on existiting payment, together with its own recommendations, to the bureau for approval. The Bureau on its part shall revise, reorganizing and evaluating, and submit the issue to the regional government council so as to get it approved.

10. Collection of Revenue

1. Any city administration or municipality shall, pursuant to this regulation, have its own organization that assesses, collects as well as registers tax, property and service charges or other revenues.
2. Finance and local economic development office of the city administration or lead municipality in a woreda, at the level of municipality, shall have receipts published and distributed to determine or collect any kind of revenue. The Bureau shall issue a directive with regard to the detail procedure.
3. It is prohibited to collect any revenue, tax or property and service charge without official receipt of the city administration or the municipality.

11. Notification

1. Any property owner or city service beneficiary or one who is duty bound to execute tax or property and service charges as per this regulation, shall declare and pay within the specified period.
2. Any person who fails to declare and pay the tax or fee and charge shall, as per the decision of the relevant body, be made to pay the principal tax together with the penalty imposed on him pursuant to this regulation.

12. Tax Determination

1. The city council in city administrations, and the

www.abyssinialaw.com

በማዘጋጃ ቤቶች ደግሞ የማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት ግብር እና ሌሎች የዕቃና አገልግሎት ክፍያዎችን የሚፈፅሙ ሰዎች ያለባቸውን ግዴታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ግምገማና ግምት የሚያከናውን ኮሚቴ ያቋቁማል::

2. ኮሚቴው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ በዚህ ደንብ መሰረት ከግምት ውስጥ መግባት ካለባቸው ሁኔታዎች በተጨማሪ የዕቃና አገልግሎት ክፍያዎችን በትክክል ለመወሰን እንዲቻል የንብረትን ዋጋና አገልግሎቶችን ወጪ ለመገመት የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፣ዘዴዎችን ይቀይሣል::

3. የኮሚቴው አባላት ስብጥር እና ብዛት በከተማው ወይም በማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት የሚወሰን ሲሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የከተማ አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤት አስፈፃሚ አካላት፣የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ከሚመለከታቸው የህዝብ አደረጃጀቶች እንዲሁም ከንግዱ ሕብረተሰብ የሚወከሉ ባለድርሻዎችን ማካተት ይኖርበታል::

13. ስለመቀጫ

1. የሚፈለግበትን ግብር ወይም የዕቃና አገልግሎት ክፍያ በዚህ ደንብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አስታውቆ ያልከፈለ ማናቸውም ሰው በሥራ ላይ ካለው የባንክ የማበደሪያ ወለድ ጋር እኩል በሆነ ምጣኔ ከሚታሰብ ወለድ በተጨማሪ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ባልተከፈለው መጠን ላይ የሚታሰብ 1% መቀጫ ይከፍላል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚጣለው መቀጫ መከፈል ካለበት ግብር ወይም የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ ጠቅላላ መጠን 50% ሊበልጥ አይችልም::

3. የመቀጫው መታሰብ መጀመር በከተማው ገቢ ለመሰብሰብ የተፈቀደለት አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ንብረት መያዝን ጨምሮ ሌሎች እርምጃዎችን ከመውሰድ አያግደውም::

4. የከተማ አስተዳደሩ ወይም ማዘጋጃ ቤቱ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የሚፈለግበትን ግብር

municipal council in municipalities shall establish a committee that carries out evaluation and assessment which is capable of ensuring those people who have the obligation to execute tax and other property and service charges.

2. Where the committee carries out its duty, it shall, besides those circumstances taken into account pursuant to this regulation, undertake a study, and devise mechanisms which enable to estimate property value and services charges so as to determine property and service charges correctly.

3. Composition and number of the members the committee shall, being determinable by the city or municipal council, include representatives from the concerned executive bodies of city administration or municipality, from government offices, and the concerned civic organizations as well as from the business community share holders.

13. Penalty

1. Any person who has failed to declare and pay the tax, or property and service charges expected from him/her within the period specified in this regulation, shall pay 1% penalty to be calculated against unpaid amount, for delay of each month, inaddition to the interest that is equivalent to the current bank loan interest.

2. The penalty to be imposed pursuant to sub art (1) of this article hereof may not exceed 50% of the total amount of payable tax or property and service charge.

3. The commencement of penalty may not waive the body who is authorized to collect income in the city from holding property as a guarantee including taking any other measures pursuant to sub- art. 4 of this article hereof.

4. The city administration or municipality shall have the power to hold the property of a person who has

www.abyssinialaw.com

እና የዕቃና አገልግሎት ክፍያ ያልከፈለን ሰው ንብርት በመያዝ ለዕዳው ክፍያ የማዋል ሥልጣን አለው:: ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል::

5. ግዴታውን ካልተወጣ ማንኛውም ሰው ላይ ገቢን ለመሰብሰብ የተደረገውን ማናቸውንም ወጪ ግዴታውን ያልተወጣው ሰው እንዲተካ ይደረጋል::

14. ስለይግባኝ

1. በኮሚቴው በተሰጠው የግብር ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ግብር ከፋይ በቢሮው በሚወጣ መመሪያ ለሚቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ከተጣለበት ግብር ውስጥ 50% ቱን በቅድሚያ አስይዞ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል::
2. ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ግብር ከፋይ የህግ ግድፈት አለበት ብሎ ካመነ ውሣኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት ወይም ይህ ባልተቋቋመበት ስፍራ ከባቢያዊ ሥልጣን ላለው የወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ሊያስወስን ይችላል::

15. ገቢ ስለማድረግ

በዚህ ደንብ መሰረት ገቢ እንዲሰበስብ የተፈቀደለት ማናቸውም አካል የሰበሰበውን ወይም የተቀበለውን ወይም የተፈፀመለትን ማናቸውም ክፍያ በየቀኑ የሥራ ሰዓት ማብቂያ በከተማው ባለው ዋና የባንክ ሂሣብ ገቢ ማድረግ አለበት:: የባንክ አገልግሎት በሌላቸው ከተሞች ገንዘቡ ከብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ እስካልበለጠ ድረስ በአካባቢው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም ጽ/ቤቱ በሌለበት ሁኔታ በራሣቸው የተጠናከረ ካዝና እየተጠበቀ በጊዜያዊነት ሊያስቀምጥ ይችላል:: ዝርዝር አሠራሩ በመመሪያ ይወሰናል::

16. ስለምዝገባ

1. ማናቸውም የከተማ አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤት ሂሣብ የከተማውን የፋይናንስ አስተዳደር ልዩ ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት እና

failed to pay the tax as well as property and service charge needed from him within the specified period and allot same to compensate his debt thereof. The detail shall be determined by a directive.

6. Any person who has failed to discharge his obligation shall be made to sustitute the expense incurred to collect revenue from him due to that effect.

14. Appeal

1. Any tax payer who is dissatisfied with the tax decision made by the committee shall submit its complaint to the appeal hearing committee, to be established according to the directive to be issued by the Bureau, with prior submission of 50% the tax imposed on him as a gurantee.
2. Any tax payer who is dissatisfied with the decision of the appeal hearing committee, believing that wrong being committed, shall submit the matter within 30 days of receiving same to city focus affairs court or on the absence of such, to an authorized woreda court of the locality and have it decided thereon.

15. Depositing

Any body who is authorized to collect revenue pursuant to this regulation shall deposit the money he has collected or received or any payment executed for him in the main bank account of the town at the end of each working day. On those towns where there is no bank service, he may deposit in the local finance and economic development office or, in the absence of such, he may temporarily deposit in their own secured coffer being watched provided that the amount does not exceed 10,000 (ten thousand birr). The detail shall be determined by a directive.

16. Record

1. Any finance of city administration or municipality shall be recorded taking the special characteristics of the city into account and pursuant to finance

www.abyssinialaw.com

ክልላዊም ሆነ ፌዴራላዊ የሂሣብ አመዘጋገብ ስርዓቶችን ባገናዘበ መንገድ በተዘጋጀው የሂሣብ አወቃቀር ሥርዓት መሰረት ይመዘገባል:: ዝርዝሩ ቢሮው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አስተያየት ታግዞ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

2. በዓይነት የተገኘ ማናቸውም ዕርዳታ ዋጋ ግምት በከተማው አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት ሂሣብ ውስጥ መመዝገብ ይኖርበታል::

17. ስለባንክ ሂሣብ

1. ማናቸውም የከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት እንደአስፈላጊነቱ የከተማው ገቢዎች ተቀማጭ የሚደረጉበት ቢያንስ አንድ የባንክ ሂሣብ በስሙ እንዲከፈት ያደርጋል:: ይሁን እንጅ ሁኔታዎች ሲያስገድዱና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተማው ስም ከአንድ በላይ የሆኑ ዋና ሂሣቦችን ከመክፈት አይከለከልም::
2. በከተማ አስተዳደር ደረጃ ባሉ ከተሞች የተደራጁ ልዩ ልዩ አስፈፃሚ አካላት የሚያስተዳድሩትን በጀት የሚያንቀሣቅሱበት የራሣቸው ሂሣብ በየመስሪያ ቤታቸው ስም ወይም በጋራ ሊከፍቱ ይችላሉ::
3. ማናቸውም የከተማው አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት:-
   ሀ. ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ ባንኮች
   ለ. በባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 በተደነገገው መሰረት የባንክ ሥራ እንዲሰሩ ከተፈቀደላቸው ተቋማት ውጪ የባንክ ሂሣብ መክፈት አይችልም::
4. የከተማ አስተዳደሩ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ስለከተማ አስተዳደሩ ሂሣቦች አከፋፈትና እንቅስቃሴዎች ይህንን ደንብ መሰረት አድርጐ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::
5. አስፈፃሚ አካላት በየወሩ ያደረጉትን የገንዘብ እንቅስቃሴ ለምዝገባና ለስታስቲክስ አላማ ያገለግል ዘንድ ለገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል::
6. የከተማው አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት የተቀበለው ማናቸውም ገንዘብ በዚህ ደንብ

organization system which is prepared considering Regional and Federal financial bookkeeping systems. The detail shall be determined by a directive to be issued by the Bureau upon the recommendation of the Finance and Economic Development Bureau.

2. An estimate of value of any aid in kind shall be recorded in the account of the city administration or the municipality.

17. Bank Account

1. Any city administration or municipality shall, as may be necessary, at least one bank account open in its name to deposit the revenue of the city; provided, however, that, where circumstances so require and found necessary, opening more than one main accounts in the name of the city it shall not be prohibited.
2. Various executive bodies organized in the towns which are at the level of city administration may open their own separate account either in the name of each respective office, or jointly so as to run the budget they are administering.
3. Any city administration or municipality may not open bank account:
   A. In banks outside Ethiopia;
   B. Out of those institutions that are authorized to undertake bank activities pursuant to the provision of bank proclamation No. 83/1993.
4. The finance and economic development office of the city administration may, on the basis of this regulation, issue a directive with regard to account opening and activities of the city administration.
5. Executive bodies shall report the finanancial transactions they made every month to the finance and local economic development office so as to make the former serve for the purpose of registration and statistics.
6. Any fund that the city administration or municipality has received shall, pursuant to the

www.abyssinialaw.com

በተደነገገው መሰረት አግባብ ባለው የባንክ ሂሣብ ውስጥ ወዲያውኑ ገቢ መደረግ አለበት።

7. የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወሩ በተጠናቀቀ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ፣ በወሩ ውስጥ የተሰበሰበውን እና ከባንክ ወጪ የተደረገውን ሂሣብ የሚያሣይ የተጠቃለለ ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል።

8. በማዘጋጃ ቤት ከተሞች የማዘጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወሩ በተጠናቀቀ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ በወሩ ውስጥ የተሰበሰበውን እና ከባንክ ወጪ የተደረገውን ሂሣብ የሚያሣይ የተጠቃለለ ሪፖርት ለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤቱ ያቀርባል።

9. በበጀት ዓመቱ ውስጥ የባንክ ሂሣብ የከፈተ ወይም ከፍቶ የነበረ የከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካል ወይም የሥራ ክፍል፣ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ30 ቀናት ውስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያጠቃልል መረጃ ለገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ያቀርባል፡-

   ሀ. የባንክ ሂሣቡን ዓይነት እና ቁጥር፣
   ለ. በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ እና መጨረሻ በባንክ ሂሣቡ ውስጥ የሚታየውን መነሻና ቀሪ ሚዛን።

10. በማዘጋጃ ቤት ደረጃ ያሉ ከተሞችም ያላቸውን የባንክ አንቅስቃሴ በተመሣሣይ መንገድ ለሚመለከተው ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ያሣውቃሉ።

ክፍል ሶስት
በክፍፍል ስለሚገኝ ገቢና የመንግስት ድጋፍ

18. በክፍፍል ስለሚገኝ ገቢ

1. የክልሉ መንግስት ከጊዜ ወደ ጊዜ በጋራ የፋይናንስ ቦርድ ተዘጋጅቶ በሚቀርበውና በመንግሥት በሚፀድቀው የገቢ ክፍፍል ቀመር መሰረት የሚመደበውን ድርሻ በከተማ አስተዳደር ደረጃ ላሉ ከተሞች ያስተላልፋል። በወረዳ አስተዳደሮችና በማዘጋጃ ቤት ከተሞች መካከል ሊኖር የሚገባውንም የበጀት ክፍፍል

provision of this regulation, be deposited forthwith in a relevant bank account.

7. The finance and local economic development office of the city shall submit a consolidated report to the mayor within 15 days after the month is over, showing the fund collected and withdrawn from the bank within the month.

8. The municipality manager in municipal towns shall submit a consolidate report to the woreda administrative council within 15 days after the month is over showng the fund collected and withdrawn from the bank within the month.

9. An executive body of a city administration or work division that used to open a bank account in the fiscal year shall submit information containing the undermentioned points to the finance and economic development office within 30 days after the fisical year is over:

   A. The type and number of the bank account;
   B. The initial and the ending balance of the bank account shown at the beginning and the end of the fiscal year.

10. Towns at the municipality level shall also notity their bank statement in a similar way to the concerned woreda Finance and Economic Development Office.

PART THREE
REVENUE BY SHARING AND GOVERNMENT SUBSIDY

18. Revenue Obtained in Share

1. The Regional State shall transfer the share to be submitted being prepared by common finance board from time to time and allotted, pursuant to the revenue sharing formula approved, by government to those towns which are at the level of city administration. It may also decide with regard to the possible share among the woreda

www.abyssinialaw.com

አስመልክቶ ሊወስን ይችላል::

2. የገቢ ክፍፍል ዘዴው፣ቀመሩና ዝርዝር አሰራሩ በቦርዱ ተዘጋጅቶ በክልሉ ውስጥ በሚሰራጭ ጋዜጣ ወይም በሌላ በማናቸውም አመች የመገናኛ ዘዴ በኩል ለህዝብ እንዲገለጽ ይደረጋል:: ይህ ማስታወቂያ የገቢ ክፍፍል ዘዴውን ቀመሩንና አሰራሩን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑትን ታሣቢዎች ጭምር መያዝ አለበት::
3. የጋራ የፋይናንስ ቦርድ በዚህ ደንብ መሰረት የገቢ ክፍፍል ዘዴውን፣ ቀመሩንና ዝርዝር አሠራሩን በሚያዘጋጅበት ጊዜ መሰረት የሚያደርጋቸውን መስፈርቶችና ማካተት የሚገባቸውን አመልካች ነጥቦች በየጊዜው ይፋ ያደርጋል::
4. የጋራ የፋይናንስ ቦርድ በወረዳ አስተዳደሮችና በማዘጋጃ ቤቶች መካከል ሊኖር ስለሚገባው የድጋፍና የበጀት ክፍፍል አሠራር የክልሉን መንግሥት በተጨማሪ ያማክራል::

administrations and municipal towns.

2. The revenue sharing system, the formula and the detailed procedure shall be prepared by the board and made public using a newspaper that circulates in the Region, or through any other favourable means of communication. The notice shall contain the assumptions which are the basis for the preparation of the revenue sharing system, the formula, the procedure as well.
3. The common financial board shall, pursuant to this regulation, publicize from time to time, the criteria and necessary indicator on which it may be based on in preparing the revenue sharing method, the formula, and the detail procedure.
4. The common financial board shall inaddition consult the Regional state with regard to the support and the budget sharing procedudre that have to exist between the woreda administrations and municipalities.

19. ስለድጋፍ

1. የክልሉ መንግስት ከተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ለከተማ አስተዳደሮች የካፒታል ፕሮጀክቶችን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል::
2. የጋራ የፋይናንስ ቦርድ ስለከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አቋም የሚያቀርበውን መረጃ መሰረት በማድረግ እንዲሁም የክልሉ መንግስት ሀብት ከከተሞች ውጪ ላሉ አስተዳደሮች ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ ሊደርስ መቻሉን አስቀድሞ በማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለከተማ አስተዳደሮች ሊፈቀድ የሚችለውን የድጋፍ መጠን ለክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያቀርባል::
3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቦርዱ ለፕሮጀክቶች የሥራ ማስኬጃ ወጪ የሚውልና በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ተጨማሪ ድጋፍ እንዲሰጥ ቦርዱ ለክ ልሉ መንግስት ሃሣብ ሊያቀርብ ይችላል::
4. ከክልሉ መንግስት የተገኘው ጠቅላላ ድጋፍ የጋራ የፋይናንስ ቦርድ በሚያቀርበውና

19. Assistance

1. The Regional state may provide financial assistance which enables city administrations to cover the expenditure of capital projects from the consolidated.
2. The common financial board shall, based on the information it submits concerning financial position of the city administrations as well as ascertaining, before hand, that the Regional state's resource has distributed to non-city administrations fairly, submit the amount of assistance that may be allocated to the city administrations within the fiscal year to the Regional Finance and Economic Development Bureau.
3. Where, as it may be necessary, the board may submit a proposal of operational expenditure for the projects and supplementary assistance on the basis of preconditions to the Regional state.
4. The total support obtained from the Regional state shall be shared among the city administrations

www.abyssinialaw.com

በመንግሥት በሚወስነው ቀመር መሰረት ለከተማ አስተዳደሮች ይከፋፈላል፡፡

5. የጋራ የፋይናንስ ቦርድ የድጋፍ ማከፋፈያ ቀመር በሚዘጋጅበት ጊዜ መሰረት የሚያደርጋቸውን ታሣቢዎችና መካተት የሚገባቸውን ዝርዝሮች በየጊዜው ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

6. ከክልሉ መንግስት ለከተማ አስተዳደሮች የሚተላለፈው ድጋፍ በቅድመ ሁኔታ እና በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ በጥቅል የሚሰጥ ወይም በተለዩ ሁኔታ በቅድመ ሁኔታ እና በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል፡፡

7. የጋራ የፋይናንስ ቦርድ ለከተማ አስተዳደሮች ጥቅል ወይም የተለየ ደጋፍ ለማከፋፈል ይቻል ዘንድ ለክልሉ መንግስት በሚያቀርበው አስተያየት ውስጥ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

   ሀ. ፍትሃዊነት፣
   ለ. የመፈፀም ብቃት
   ሐ. መሰረታዊ የማስፈፀም አቅም አናሣነት
   መ. አስተማማኝነት፣
   ሠ. አበረታችነትና፣
   ረ. በወረዳና በማዘጋጃ ቤት ከተሞች መካከል ያለ የልማት ትስስርና የግንኙነት ደረጃ፣
   ሰ. የከተሞች የመልማት ዕድልና ለእድገት ማዕከልነት ተመቻችቶ መገኘት፡፡

pursuant to the formula to be presented by the common financial board and determined by the state.

5. Where the common financial board designs support sharing formula, it shall occasionally publicize the assumptions the formula is based on and the details which should be incorporated.

6. The support to be transferred to city administrations from the Regional state may be granted in total, without preconditions and requirements, or may be on preconditions and requirements in a special case.

7. The common financial board shall take the following into account in the recommendations it may submit to the Regional state so as to be able to share total or special support among city administrations:

   A. Fairness;
   B. Implementation capacity;
   C. Lack of basic implementing cpacity;
   D. Reliability;
   E. Encouragement;
   F. Development connection and relational status between woreda and municipal towns;
   G. Developing potential of twons and their being favourable as development center.

20. ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ ስለማስፈለጉ

የገቢ ክፍፍል እና ድጋፍ አሰጣጥ ዘዴዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ሁሉ በከተማ አስተዳደሮች፣ በአነስተኛ ከተሞችና በገጠር ወረዳዎች መካከል ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ድልድል ወይም ክፍፍል መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት መፈጠርና ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡

20. Necessity of Ensuring Equity

There shall be created and put into effect a working procedure which enables to ensureequitable resource allotment or sharing amongst all city administrations, small towns and rural woredas when revenue sharing and support providing methods are designed.

ክፍል አራት
ስለብድር

PART FOUR
LOAN

21.ጠቅላላ

1. በከተማ አስተዳደር ደረጃ የተደራጁ ከተሞች

21. General

1. Any short and long term loan, which those cities

www.abyssinialaw.com

የሚወሰዱት ማናቸውም የአጭርና የረዥም ጊዜ ብድር አገራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን እና የገንዘብ ፖሊሲን የማይነካ መሆን ይኖርበታል፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም ማናቸውም የከተማ አስተዳደር የማይጠይቀውን ብድር ከመውሰዱ በፊት አስቀድሞ የወሰደውን ዕዳ ክምችት፣ ሊወሰድ የታሰበውን ብድር መጠን እና የሚውልበትን ዓላማ ለክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ማስታወቅ አለበት፡፡

3. በከተማ ደረጃ የሚቋቋሙ የልማት ድርጅቶች በራሳቸው የመበደር ስልጣን ያላቸው ሲሆን የብድራቸው ሁኔታም ድርጅቶቹ ከአበዳሪ አካላቱ ጋር በሚደርሱበት ስምምነት መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

22.የአጭር ጊዜ ብድር

1. ማናቸውም የከተማ አስተዳደር የአጭር ጊዜ ብድር ወይም ቀጥታ ብድር ሊወሰድ የሚችለው ከቦርዱ የሚቀርበው ሀሳብ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት እና በንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮዎች በጋራ ታይቶ ሲፀድቅ እና በሚከተሉት ምክንያቶች የሚያጋጥምን የገንዘብ እጥረት ለማሟላት ይሆናል፡፡
   - ሀ/ ብድሩ በሚወሰድበት የበጀት ዓመት ያጋጠመን የገንዘብ እጥረት ለማሟላት ሆኖ በዚያው የበጀት ዓመት ዕዳውን መልሶ ለመክፈል የሚያስችል ተለይቶ የታወቀ እና የተረጋገጠ ገቢ የሚገኝ መሆኑ የሚጠበቅ ሲሆን፣
   - ለ/ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለካፒታል ወጪ ፍላጐት ማሟያ የሚውል የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም እና በብድር የተወሰደው ገንዘብ ተለይቶ ከታወቀን በሕግ ከተፈቀደ ድልድል ወይም ከረዥም ጊዜ ብድር ከሚገኝ ገንዘብ በዚያው የበጀት ዓመት ውስጥ ተመልሶ የሚከፈል ሲሆን፣

organized at city administration level cities take, shall not affect the National Macro-Eonomic stability as well as the Finance policy.

2. For the execution of sub art (1) of this article, any city administration shall notify the Regional Finance and Economic Development Bureau of its total previous debt, the amount of loan it expects and the purpose the loan serves before taking the requested loan.

3. Development enterprises to be established at city level shall have the authority to borrow by themselves, and the condition of their loan shall be determined pursuant to the agreement enterprises reach with loan rendering bodies.

22. Short Term Loan

1. Any city administration may be able to take short term or direct loan on conditions that the recommendation of the board is approved by the Regional Finance and Economic Development and Trade, Industry and Urban Development Bureax jointly and to fulfil the shortage of fund that may be faced due to the following reasons:
   - A. With the view to fulfiling the fund shortage faced in the budget year thereof, and where it is believed that definite and reliable revenue which enables to refund the debt in the same fiscal year is expected;
   - B. Where there is shortage of fund to meet the demand of capital expenditure, and the fund taken on laon can be refunded within the same fiscal year from legally appropriated definite amount, or from long term loan;

www.abyssinialaw.com

ሐ/ የብድር ስምምነቱ በከተማው ምክር ቤት ውሣኔ ሲፀድቅ እና ይኸው ውሣኔ በከተማው ከንቲባ ፊርማ ሲረጋገጥ፣

መ/ የሚመለከተው ከተማ የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ የብድር ስምምነቱን ወይም ብድሩ የተወሰደ መሆኑን የሚያረጋግጡ ወይም ለዕዳው ዕውቅና የሚሰጡ ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶችን በከተማው አስተዳደር ስም ሲፈርም፡፡

2. ብድሩ የተገኘው ከአንድ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ጋር በተደረገ ስምምነት ሆኖ፣ የብድሩ ጣሪያ በሚያፀድቀው ምክር ቤት ተወስኖ በአንድ ጊዜ ብድር ወይም እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው በሚወሰዱ ብድሮች ሲሆን፣ የክፍያው ጊዜ ሊሻሻል የሚችለው ብድሩን ባፀደቀው ምክር ቤት በሚሰጥ ውሣኔ ብቻ ይሆናል፡፡

3. ምክር ቤቱ ያፀደቀው ብድር አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን፣ የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በተቻለ አጭር ጊዜ ውስጥ የተገባውን ዕዳ መጠን፣ ብድሩ የሚያስከትለውን ወጪ፣ የዕዳውን ክፍያ ለመፈፀም ከሚያስችሉ አማራጮች ጋር ለምክር ቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. የከተማው አስተዳደር፣

ሀ/ የወሰደውን የአጭር ጊዜ ብድር በተወሰደበት የበጀት ዓመት ውስጥ መልሶ መክፈል አለበት፣

ለ/ የከተማውን አስተዳደር ወይም ዋስትና የተሰጠበትን የሌላ አካል ብድር መልሶ መክፈያ ጊዜ ወደሌላ የበጀት ዓመት የማሸጋገር ውጤት በሚኖረው አኳኋን ውሉን ማሻሻል ወይም ዕዳውን ለመክፈል የሚያስችል ሌላ ብድር መውሰድ አይችልም፡፡

23. የረዥም ጊዜ ብድር

C. Where the loan agreement is endorsed by the city council and verified by the signature of the mayor;

D. Where head of Finance and Local Economic Development Office verifies, in the name of city administration, the loan agreement or that loan has been taken, or he signs other similar documents recognizing the liability.

2. Where the loan is obtained upon agreement made with an individual, a group or an organization, the loan celling is determined by the endorsing council and is taken once or, as may be appropriate, at different times, the laon period may be amended only by the decision of the loan endorsing council.

3. Where urgent circumstances encounter, the loan endorsed by the council is put in to effect and the city Finance and Local Economic Development Office shall, within a short possible period, notify the council of the amount of debt incurred, the expenditure caused due to the debt with those alternatives enabling to repay the debt.

4. The city administration:

A. Shall refund the short term loan it has taken within the fiscal year the loan has been taken;

B. May not amend the loan accord, having refunded the loan of the city administration, or of other organ's secured loan, in a way that it may have an effect of shifting the maturity date to another fiscal year, nor take another loan for the redemption of former loan.

23. Long -Term Loan

www.abyssinialaw.com

1. ማንኛውም የከተማ አስተዳደር የረዥም ጊዜ ብድር ሊወስድ የሚችለው ከቦርዱ የሚቀርበው ሀሳብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ታይቶ ሲፀድቅ ሆኖ፣ ለሚከተሉት ዓላማዎች ማስፈፀሚያ የሚውል ለመሆኑ አስቀድሞ ሲረጋገጥ ነው፦
   - ሀ/ የከተማው አስተዳደር የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መሠረተ ልማት ማስፋፊያ፣ የግንባታና የልማት ስራዎች ማከናወኛ፣ ለኢንቨስትመንት ስራዎች ማካሄጃና ቋሚ ንብረቶች ማምረቻ ወይም ሌሎች መሣሪያዎች ማፍሪያ ለሚያስፈልጉ የካፒታል ወጪዎች፣
   - ለ/ አስቀድሞ የተወሰደን የረዥም ጊዜ ብድር ክፍያ ለመፈፀም፡፡
2. የተጠቀሰው የረጅም ጊዜ ብድር በዚህ ደንብ መሰረት ተወስዷል የሚባለው ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፦
   - ሀ/ የብድር ስምምነቱ በከንቲባ ኮሚቴው ውሳኔ ሲፀድቅና በከተማው ከንቲባ ፊርማ ሲረጋገጥ፣
   - ለ/ የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የብድር ስምምነቱን ወይም ብድሩ የተወሰደ መሆኑን የሚያረጋግጡ ወይም ለዕዳው ዕውቅና የሚሰጡ ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶችን ሲፈርም፡፡
3. የከተማው ምክር ቤት ብድሩን ለማፅደቅ ስብሰባ ከሚያካሂድበት ዕለት ቢያንስ 15 የሥራ ቀናት በፊት የሚወሰደውን ብድር እና የሚሰጠውን መያዣ ዝርዝር የሚያመለክት መግለጫ በገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በኩል ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
4. የከተማው ነዋሪ ህዝብ ሊፈረም የታሰበውን የብድር ስምምነት በተመለከተ ያለውን አስተያየት በፅሑፍ ወይም በአካል በመገኘት ለምክር ቤቱ እንዲደርስ የማድረግ መብት ይኖረዋል፡፡

1. Any city administration may take long term loan where the recommendation from the board is reviewed and approved by the council of the Regional state, and is confirmed, before hand, that it serves for the execution of the following objects:
   - A. Capital expenditure necessary for the expantion of infrastructure, accomplishment of construction and development activities, undertaking investment activities as well as production of fixed assests or other equipment enabling to attain the establishing objective of the city administration;
   - B. To redeem the long-term loan taken previously.
2. The specified long term loan is, pursuant to this regulation, said to be taken where the conditions indicated hereinunder are fulfilled:
   - A. Where the loan agreement is endorsed by the decision of the mayoral committee and ratified by the signature of the city mayor;
   - B. Where the City Finaice and Local Economic Development Office signs loan accord, or the documents that confirm the loan has been taken or that give recongnition to the debt thereof.
3. The city council shall, at least 15 working days prior to undertaking meeting to endorse the laon, notify the public through the Finance and Economic Development Office of the detailed explanation of the loan it wants to take and the guarantee to be pawned.
4. The residents of the city shall have the right to submit their comments to the city council in writing or in person with regard to the loan agreement thought to be signed.

www.abyssinialaw.com

5. የከተማው ገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የምክር ቤቱ ስብሰባ ከሚካሄድበት ዕለት ቢያንስ 15 የስራ ቀናት ቀደም ብሎ የብድር ስምምነቱን ቅጅና የብድሩ ገንዘብ ተመልሶ እስኪከፈል ድረስ ይከተላሉ ተብለው የሚገመቱ ወጪዎችን የሚያሣይ ዝርዝር በከንቲባው በኩል ለከተማው ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡
6. ማንኛውም የከተማ አስተዳደር ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላታቸውን አረጋግጦ ቀድሞ የተወሰደን ብድር ለመክፈል የሚያስችል ሁለተኛ ብደር ሊወስድ ይችላል፡-
   ሀ/ አስቀድሞ የተወሰደው የረዥም ጊዜ ብድር በሕግ መሠረት የተወሰደ ሲሆን፣
   ለ/ ብድሩን ለመክፈል የሚወሰደው ብድር የመክፈያ ጊዜው በመጀመሪያው ብድር በተወሰደው ገንዘብ ከተከናወኑ የልማት ስራዎች ከተገዙት ንብረቶች፣ የማምረቻ ወይም ሌሎች መሣሪያዎች የጠቀሜታ ጊዜ በላይ ካልሆነ፣
   ሐ/ ብድሩን ለመክፈል የተወሰደው ገንዘብ የወደፊት ክፍያ የዋና ገንዘቡንና የወለድ ክፍያውን ጨምሮ የተጣራ የአሁን ጊዜ እሴት፣ በቀድሞው ስምምነት መሠረት ሊፈፀም ከታሰበው የወደፊት ክፍያ የተጣራ የአሁን ጊዜ እሴት የሚያንስ ሲሆን፣ እና
   መ/ በፊደል ተራ ቁጥር (ሐ) ከተጠቀሰው የተጣራ የአሁን ጊዜ እሴት ላይ ለመድረስ ሥራ ላይ የዋለው የማቀናነሻ ምጣኔ እና ስሌቱ መሠረት ያደረጋቸው ሌሎች ታሳቢዎች የተደገፉ እና ወደፊት ሥራ ላይ በሚውለው ማዕቀፍ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟሉ መሆን ሲሆን፡፡
7. ማናቸውም የከተማ አስተዳደር የሚወስደው የረዥም ጊዜ ብድር በዓመታዊው የክልሉ መንግሥት በጀት ውስጥ የካፒታል በጀት ድርሻን ለመወሰን ሥራ ላይ ከዋለው መርህ ጋር የተጣጣመ

5. The city Finance and Lcoal Economic Development Office shall have the responsibility to submit, at least 15 working days before the meeting of the council undertakes, a copy of the loan accord and a list that shows the expenditures expected to occur upto the period the loan is to be redeemed, to the city council through the mayor.
6. Any city administration may, having ascertained that the undermentioned requirements are met, take second loan to redeem a previous loan:
   A. Where it is proved that the previous long term loan was taken in accordance with law;
   B. Where the due period of the loan to be taken so as to pay the previous one does not exceed the useful life of properties, production and other equipment procured as part of developmental activities performed with the loan taken previously;
   C. Where the current net value of the future repayment, including the principal and interest accrued, of loan to be taken to redeem the previous loan is less than the current net value of the future redemption that was thought to be made pursuant to the previous loan accord, and
   D. Where the deducting amount implemented to reach at the current net value indicated under letter (C) and supoorted by other assumptions that the formula bases as well as fulfill the criteria indicated in the framework that may be implemented in the future.
7. The long-term loan that any city administration takes shall be in harmony with the principle implemented to determine the share of capital budget in the annual buget of the Regional state.

www.abyssinialaw.com

መሆን ይኖርበታል፡፡

24. ለአጭር እና ለረዥም ጊዜ ብድር በጋራ የሚያገለግሉ ሁኔታዎች

የከተማ አስተዳደር በዚህ ደንብ መሰረት የሚወስደው የአጭርም ሆነ የረጅም ጊዜ ብድር በኢትዮጵያ ብር ሆኖ በየጊዜው መዋዠቅ ከሚታይባቸው የውጭ ሃገር ገንዘቦች ጋር ያልተያያዘ ወይም በእነዚሁ ተፅዕኖ ስር የማይወድቅ መሆን አለበት፡፡

25. ስለመያዣ

1. የከተማው አስተዳደር የከተማው ምክር ቤት በሚወስነው መሠረትን፦
   - ሀ/ የከተማው አስተዳደር ለገባው ማናቸውም የብድር ግዴታ፣
   - ለ/ በከተማው አስተዳደር ብቸኛ ቁጥጥር ሥር ያለ የልማት ድርጅት ለገባው ማናቸውም የብድር ግዴታ፣
   - ሐ/ የከተማው አስተዳደር በውል በገባው ግዴታ መሠረት ለሚጠቀምባቸው ወይም የከተማውን አስተዳደር ዓላማ ለማስፈፀም ሌላ ሰው ለሚጠቀምባቸው ንብረቶች፣ የማምረቻ እና ሌሎች መሣሪያዎች ሌላ ሰው ለሚፈፅመው የካፒታል ወጪ፣ መያዣ መስጠት ይችላል፡፡
2. የከተማው አስተዳደር ለሚበደረው ብድር የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች ተገቢ የሆኑ መያዣዎችን ዋስትና አድርጎ ሊሰጥ ይችላል፡፡
   - ሀ/ ሀብትን በዋስትና፣ በመያዣ ወይም በሌላ ተመሳሳይ የመያዣ ውል በመስጠት፣
   - ለ/ ወደፊት ይገኛል ተብሎ ከሚገመት ገንዘብ ወይም ሀብት እንዲከፈል ግዴታ መግባት ወይም አበዳሪው ወይም ኢንቬስተሩ እንደዚህ ያሉ ገቢዎችን በቀጥታ እንዲወስድ በመፍቀድ ዕዳው የሚከፈል መሆኑን ወይም መያዣ የተሰጠበት ግዴታ የሚፈፀም መሆኑን

24. Condtions Commnly Serving Short and Long Term Loans

The long and short term loan that the city administration takes pursuant to this regulation shall be in Ethiopia Birr, and should not relate to or be influenced by occasionally fluctuating foreign currencies.

25. Guarantee

1. The city administration shall, pursuant to the decision of the city council, offer guarantee to:
   - A. Any loan obligation that the city administration entered in to;
   - B. Any loan commitment that an enterprise under the sole jurisdiction of the city administration entered in to;
   - C. The properties that the city administration or other person uses as per its commetments or to implement the purpose of the city administration respectively as well as producing other instruments and capital expenditures used by another person.
2. The city administration may offer the following including other appropriate guarantees as security of the loan:
   - A. By offering property in the form of guarantee, security or other similar loan agreements;
   - B. From expected income, or committing to pay the debts in property, or assuring that the debts will be paid back by allowing the lender/investor to take such incomes directly, or guaranteed obligations shall be practical;

www.abyssinialaw.com

በማረጋገጥ፣

ሐ/ በአበዳሪው፣ በኢንቬስተሩ ወይም በሦስተኛ ወገን ዘንድ በዋስትና መልክ ገንዘብ በማስያዝ፣

መ/ ማናቸውንም የገቢ ዓይነት ወይም ወደፊት የሚሰበሰብ ገቢ ለዕዳው ክፍያ እንዳይውል ክልከላ የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ፣

ሠ/ በመደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት፡ የመጨረሻ አማራጭ እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ያለመግባባት በዕርቅ፣ በግልግል ወይም ያለመግባባትን ለመፍታት በሚያስችል ዘዴ እንዲፈታ ግዴታ በመግባት፣

ረ/ የተገባውን ግዴታ መወጣት በሚያስችል መጠን ከጠቅላላ ገቢ ቀንሶ በመያዝ ወይም የተለየ የዕቃና አገልግሎት ክፍያ ወይም ተቀማጭ ገንዘብ በተወሰነ መጠን ለዕዳው እንዲውል ግዴታ በመግባት፣

ሰ/ ዋና ገንዘብ እና ወለድን ጨምሮ ለማናቸውም ሌላ ዕዳ ክፍያ የሚውል ገንዘብ በበጀት በማስያዝ፣

ሸ/ በመያዣነት ብድር የተወሰደበት ማንኛውም ሀብት ዕዳው ከመወራረዱ ወይም ተከፍሎ ከማለቁ በፊት የከተማው አስተዳደር ወደፊት ሌላ ብድር የማይወስድ ስለመሆኑ ግዴታ በመግባት፣

ቀ/ የከተማው አስተዳደር አስፈላጊና ተገቢ ናቸው ብሎ በሚያምንባቸው ሌሎች ዘዴዎች በመስማማት፣

3. መያዣ የሚፈቅድ ማናቸውም የከተማው ምክር ቤት ውሣኔ፣

ሀ/ በመያዣ እንዲሰጥ የተፈቀደው ሀብት ወይም መብት መሠረታዊ የሆኑ የከተማ አስተዳደር አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚኖረውን አስፈላጊነት መወሰን፣

ለ/ መሠረታዊ የሆኑ የከተማ አስተዳደር አገልግሎቶችን ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን ይህ ሀብት ወይም መብት መሠረታዊ የሆኑ አገልግሎቶች

C. Offering fund as a guarantee to the lender, to the investor or to the third party;

D. By ensuring that no prohibition of paying back the debts out of any type of revenue or receivable fund;

E. Without prejudice to the last alternative of judgment of the ordinary court, being in debt for obligation, to resolve any dispute by reconciliation, mediation or a method enabling to solve the disagreement;

F. By holding a certain amount enabling to discharge the obligation enetered into deducting from the total revenue, or pledging to payback the debt out of special fees and charges or reserved fund;

G. By causing the allocation of fund in the budget that serves to pay back any other loan including the principal and the interest;

H. By entering into obligation that the city administration shall not take another loan before the accounting or completion of the payment of the debt using the property which already taken as a guarantee to take previous loan;

I. By giving one's consent to other methods that the city administration belives in as necessary and appropriate.

3. Decision of any city council that allows a gurantee shall:

A. Determine the necessity of the property or right allowed to be offered as a guarantee in providing city administrative services.

B. Show the condition in which the property or the right, which is believed to be essential to render basic service of city administration, shall be kept in a way that enables the basic

www.abyssinialaw.com

ሳይቋረጡ እንዲከናወኑ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

4. የምክር ቤቱ ውሣኔ ሀብቱ ወይም መብቱ መሠረታዊ የሆኑ የከተማ አስተዳደር አገልግሎቶችን ለመስጠት አስፈላጊ ነው የሚል በሚሆንበት ጊዜ በከተማው አስተዳደር መያዣ የተሰጠው ማናቸውም ተዋዋይ ወይም የተዋዋዩ ወራሽ ወይም መብቱ የተላለፈለት ወገን የከተማው አስተዳደር ግዴታውን ሳይወጣ ሲቀር፣ በሀብቱ ወይም በመብቱ ሊጠቀም የሚችለው መሠረታዊ የሆኑ የከተማ አስተዳደር አገልግሎቶች ቀጣይነት በማይደናቀፍበት ወይም በማይታወክበት ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በምክር ቤቱ የሚሰጠው ውሣኔ ሀብቱ ወይም መብቱ መሠረታዊ የሆኑ የከተማ አስተዳደር አገልግሎቶችን ለመስጠት አስፈላጊ አይደለም የሚል በሚሆንበት ጊዜ እንደአግባብነቱ መያዣ የተሰጠበት ዕዳ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ወይም በተገባው ግዴታ መሠረት እስከሚፈፀም ድረስ የከተማው አስተዳደር በውሉ መገደዱ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

26. የከተማው አስተዳደር ስለሚሰጠው ዋስትና

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የከተማው አስተዳደር በመንግሥት አካላት ወይም በማናቸውም ሌላ ሰው ለተገቡ ግዴታዎች ወይም ዕዳ ዋስትና ሊሰጥ አይችልም፡፡

1/ በከተማው አስተዳደር ብቸኛ ቁጥጥር ሥር ያለ የልማት ድርጅት ለሚወስደው የረዥም ጊዜ ብድር የከተማው አስተዳደር ዋስትና የሚሰጠው፣

ሀ. ለዕዳው ምክንያት የሆነውን የልማት ድርጅቱን የልማት ዕቅድ የልማት

services to continue.

4. Where the council takes the decision that the property or the right is essential to render basic city administration services and the administration unfortunately fails to fulfill its obligation, the contract taker, his heir/heirness or the one to whom the right is transferred, received guarantee from the administration, can make use of the guarantee (property or right) in a way that the basic services shall not be disrupted or disturbed.

5. Where the deicision made by the council pursuant to sub art. (3) of this article claims that the property or the right is not essential to render basic city services, the city council shall, as may be relevant, continue to be under obligation until the guaranteed loan is paid back or executed pursuant to the obligation signed.

26. Gurantee to be Given by the City Administration

With the exception of the conditions indicated hereinunder, the city administration may not offer a guarantee to obligations or debt it ran into by government bodies or any other person.

1. The city administration offers guarantee for the long-term loan taken by the development enterprise which is under its sole control where:

A. The board of the development enterprise endorses the development plan of the

www.abyssinialaw.com

ድርጅቱ ቦርድ ያፀደቀው ከሆነ፣ እና

ለ. በዚህ ደንብ የከተማው አስተዳደር የሚወስደው ብድር ስለሚፈቀድበት አኳኋንና ይኸው ብድር መሠረት ስለሚያደርጋቸው የውል ቃሎችና ሁኔታዎች በተደነገገው መሠረት ምክር ቤቱ ዋስትናውን ያፀደቀ እንደሆነ ነው፡፡

2/ የከተማው አስተዳደር ማናቸውም ሌላ ሰው ለገባው ዕዳ ዋስትና ሊሰጥ የሚችለው የክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲያፀድቀው እና፣

ሀ. ዋስትናው በመሰጠቱ ምክንያት የከተማው አስተዳደር ሊያጋጥመው ይችላል ተብሎ ከሚገመተው ወጪ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ጥሬ ገንዘብ ወይም ለሌላ ዓላማ ያልተመደበ መጠባበቂያ ገንዘብ ዋስትናው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ሁሉ አስተዳደሩ ለይቶ የሚያስቀምጥ ወይም የሚይዝ ከሆነ፣ ወይም

ለ. በዚሁ ዋስትና ምክንያት የከተማው አስተዳደር ያጋጥመዋል ተብሎ በሚታሰብ ወጪ መጠን በተመዘገበ የመድን ድርጅት የተሰጠ የመድን ዋስትና የከተማው አስተዳደር የገዛና መድኑ ዋስትናው በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ እንደፀና የሚቆይ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ብቻ ነው፡፡

ክፍል 5
ዕቅድ እና በጀት

27. ዕቅድ

1. ማንኛውም የከተማው አስተዳደር በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ተከፋፍሎ የሚፈፀምና የተዋሀደ ስትራቴጂዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡ ይህ ስትራቴጂዊ ዕቅድ፣ የከተማውን የኢኮኖሚ ልማት፣ የማኅበራዊ ልማት እና የመሠረተ ልማት ዕቅድ በአንድነት የሚይዝ መሆን አለበት፡፡

enterprise as the cause of the loan; and

B. The council endorses the guarantee as per the manner whereby the city administration may be allowed to take the loan and the contractual terms as well as conditions that such a loan base, provided in this regulation.

2. The city administration may provide guarantee on the loan that any other person be in debt to, where the Regional Finance and Economic Development Bureau approves; and:

A. Where the administration separately keeps or preserves, through out the time when the guarantee stays firmly in effect, cash or provision which is proportional to the expenditures the administration is expected to encounter owing to its offering of the guarantee.

B. Where it is ascertained that the city administration has entered into an insurance contract with an accredited insurance company for an amount which is equivalent to the expenditure the administration is expected encounter due to offering the guarantee, and ensured that the insurance will remain effective through out effective period of the guarantee.

PART FIVE
PLAN AND BUDGET

27. Plan

1. Any city administration shall prepare a harmonized strategic plan that may be classified and implemented in short, medium and long-terms, such strategic paln shall consist of unified economic, social as well as infrastructural development plans of the city.

www.abyssinialaw.com

2. የተዋሀደው-መሪ ዕቅድ ከብዙዎች መካከል የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡
   ሀ/ የከተማ ገቢዎች፣
   ለ/ የመሬት አጠቃቀም፣
   ሐ/ ከተማውን መልሶ የማደስ እና መልሶ የማልማት ሥራ፣
   መ/ በተወሰኑ ዓመታት ሥራ ላይ የሚውል የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ግንባታዎች ፕሮግራም እና
   ሠ/ የመሠረተ-ልማት፣ የማኀበራዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የትራንስፖርት እና የሕዝብ ዕድገትን መጠን የሚያሳይ መቶኛ፣
3. የተዋሀደው ስትራቴጃዊ ዕቅድ በውስጡ ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን ገንዘብና ገንዘቡ የሚገኝበትን ምንጭ የያዘ መሆን አለበት፡፡
4. የተዋሀደው ስትራቴጃዊ ዕቅድ እና በተወሰኑ ዓመታት ሥራ ላይ የሚውለው ዕቅድ የሚፀድቀው በዚህ ደንብ በጀት ስለሚታይበት ሥርዓት በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-4 በተመለከተው ሁኔታ በማዘጋጃ ቤትነት የተደራጁ ከተሞችም እንደየአግባብነቱ የሚመለከታቸውን ይፈፅማሉ፡፡

28. እንደገና የሚታይበት ጊዜ

1. የከተማው አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤቱ በከተማው የተዋሀደ ስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ የተመለከተውን የፋይናንስ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ከዓመታዊ በጀት በተጨማሪ ከአምስት ዓመታት ላልበለጠ ግዜ የሚቆይ ተንከባላይ ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡
2. ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚውል ገቢ መኖሩን ለማረጋገጥ የከተማው አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤቱ የእያንዳንዱን ዓመት የፋይናንስ ፍላጐት ግምት ውስጥ የሚያስገባ የታሪፍ ማሻሻያ እንዲደረግ ለሚመለከተው የበላይ አካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ይኸው ማሻሻያ ቢዘገይ በየሁለቱ ዓመቱ አንድ ጊዜ

2. The harmonized master plan shall incorporate the following, among others:
   A. City revenues;
   B. Land use;
   C. Urban renewal and redevelopment activities;
   D. Construction programs for public services to be functional within the certain forthcoming years; and
   E. Perecentage that indicate infrastructural, social, economic, transport development and population growth rate.
3. The harmonized strategic plan shall contain sum of money necessary to implement the plan and the source of the money.
4. The harmonized strategic plan to be functional within some years shall be approved pursuant to the provision of budget allotement procedure of this regulation.
5. As per the conditions indicated under sub arts 1-4 of this article, those towns organized as municipalities shall, as may be appropriate, execute their part.

28. Period of Revision

1. The city administration or the municipality shall, inaddition to the annual budget, prepare a rolling budget that does not last for more than five years on the basis of the financial paln indicated in the harmonized plan of the city.
2. To city administration or the municipality, to ensure the availability of revenue for the execution of the plan, may submit a proposal to the concerned senior body so as to make tariff amendment taking into account the financial demand for each year. If such amendement delays, it shall be accomplished at least once in two years.

www.abyssinialaw.com

መከናወን አለበት፡፡

3. ማሻሻያው የሚያስከትለውን የማስከፈያ ምጣኔ ለመቆጣጠር የከተማው አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤቱ በዕቅድ ለተያዘው የወጪ በጀት መሸፈኛ የሚውል ገቢ የሚያመነጩ ሌሎች የገቢ ምንጮችን መፍጠር አለበት፡፡

29. የበጀት ምድብ

የከተማው አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤቱ በጀት መሠረት የሚያደርገው የወቅቱን እና ወደፊት ይገኛል ተብሎ የሚታሰበውን ገቢ ሲሆን፣ ዓላማውም የከተማው የልማትና አገልግሎት ተግባራት የብዙ ዓመታት ዕቅድ ውስጥ በጀት በተፈቀደበት የበጀት ዓመት ውስጥ ይፈፀማል ተብሎ የተያዘውንና የካፒታልና የመደበኛ በጀት አንድ ክፍል የሆነውን ወጪ ለመሸፈን ነው፡፡

30. የወጪ አሸፋፈን

የዓመታዊ በጀት ወጪ የሚሸፈነው፡፡

ሀ/ በእርግጠኝነት ይሰበሰባል ተብሎ ከሚታሰበው ገቢ፣

ለ/ ለሌሎች ዓላማዎች ካልተያዘ እና ቀደም ባሉ ዓመታት ጥቅም ላይ ሳይውል ከቆየ ተራፊ ገንዘብ፣

ሐ/ ለካፒታል በጀት ብቻ ከሚውል በብድር ከተገኘ ገንዘብ ፣ እና

መ/ ከእርዳታ ከሚገኝ ገቢ ይሆናል፡፡

31. የከተማ አስተዳደሮች በጀት

1. የከተማ አስተዳደሮች በጀት መሠረት የሚያደርገው በዚህ ደንብ አንቀጽ 20 መሠረት የክልሉ መንግሥት ከሚሰበስበው ገቢ ውስጥ የከተማው አስተዳደር በገቢ ክፍፍል ቀመር መሠረት የሚተላለፍለትን ገቢ፣ ዕርዳታ፣ ድጋፍ፣ ብድር፣ ዕርዳታዎች እና የከተማ አገልግሎት ከሆኑና ካልሆኑ አገልግሎቶች ከጊዜ ወደጊዜ ከሚወሰኑና ከሚገኙ ገቢዎችና ታክሶች የአገልግሎት ክፍያዎች የሚገኝን ገቢ ይሆናል፡፡

3. The city administration or the municipality shall devise other source of income that generate revenue to cover the planned budget of expenditure so as to control the rate of payment caused by an amendement.

29. Budget Allotement

The budget of the city administration or the municipality is based on the current and forecast revenue, and its purpose is to cover the expenditure palnned to be implemented within the fiscal year of the budget appropriation and a part of capital and recurrent budget within the long term paln of the city's developmental and service activites.

30. Coverage of Expenditure

Annual budget expenditure shall be covered from:

A. Certain forecast revenue;

B. Surplus money which is not engaged for other purposes and was remained unused during the previous years;

C. The fund obtained by loan, and serve only for capital budget; and

D. Revenue to be obtained from aid.

31. City Administration Budget

1. The budget of city administrations, pursuant to Article 20 of this regulation, is based on revenue, transferred to them as per the revenue sharing formula from the revenue the Regional State Collects, on grants, support, loan and revenues available from city and non-city services, incomes and taxes determined from time to time, service charges as well.

www.abyssinialaw.com

2. የከተማ አስተዳደሮች በጀት ዝግጅት መነሻው ከፕሮግራም እና ከወጪ ማዕከል ሲሆን፣ ዝግጅቱም በየጽ/ቤት ኃላፊዎች ደረጃ የሚቀነባበር ይሆናል፡፡
3. የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ልማት ጽ/ቤት ከየጽሕፈት ቤቶች ተጠናቅሮ የሚቀርብለትን የበጀት ጥያቄ ካጠቃለለ በኋላ ከኢኮኖሚ ትንታኔ እና ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ሊወሰዱ ከሚገባቸው እርምጃዎች እንዲሁም ከሌሎችም አስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎች ጋር ለከንቲባው ያቀርባል፡፡
4. የከተማው ከንቲባ ከገንዘብና አካባቢ አኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የቀረበለትን ረቂቅ በጀት መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለከተማው ምክር ቤት እንዲፀድቅ ያቀርባል፡፡ ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይገለፃል፡፡

32. የማዘጋጃ ቤት በጀት

1. የማዘጋጃ ቤት በጀት መሠረት የሚያደርገው የማዘጋጃ ቤት የገቢ ምንጮች ከሆኑ ታክሶች፣ የዕቃና አገልግሎት ክፍያዎች ወረዳው ከሚያገኘው ገቢ ወይም ከሚመደብለት በጀት ውስጥ ለማዘጋጃ ቤቱ በክፍፍል ቀመር መሠረት የሚተላለፍለትንና ከሌሎችም ምንጮች የሚገኙትን ይጨምራል ፡፡
2. የበጀት ዝግጅት መነሻው ከፕሮግራም እና ከወጪ ማዕከል ሲሆን፣ በሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች ደረጃ የሚቀነባበር ይሆናል፡፡
3. በአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ በተጠቀሰው መሠረት የማዘጋጃ ቤቱም ምክር ቤት በስራ አስኪያጁ አማካይነት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የመሪና የየንዑስ ማዘጋጃ ቤቶችን የበጀት ጥያቄ በማጠቃለል በዝርዝር ከመረመረ በኋላ አስተያየቱን ጨምሮ እንዲፀድቅ ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

2. The start of the city administrations' budget is from the programme and expenditure cener while the preparation is organized at the level of each head of offices as well.
3. The Finance and Local Economic Development Office of the city shall, after consolidating the budget demand organized by and submitted to it from each offices, submit to the mayor with economic analysis and measures to be takent to stabilize the economy as well as with other necessary information.
4. The mayor of the icty shall examine the draft budget submitted to him form the Finance and Local Economic Development Office and submit same, to the city council with his recommendation for approval. The detail shall be prescribed by the directive to be issued by the Bureau.

32. Municipal Budget

1. The budget of a municipality is based on the taxes, property and service charges which are source of municipal income, the revenue that the woreda transfers to the municipality as per the sharing formula, and including revenues made available from other sources.
2. The start of the budget preparation is a programme and an expenditure center, and shall be organized at the level of the heads of the work units.
3. The city council shall, pursuant to the provisions of Art. (33) sub-art (5) of the proclamation, after compiling and revising the budget request of lead and sub-municipalities prepared and submitted to him by the manager, submit to the woreda council for approval including his recomendation.

www.abyssinialaw.com

33. የበጀት ጣሪያና ጉድለት

1. የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም የማዘጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የገቢውን ግምት መሠረት በማድረግ የከተማውን አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤቱን ዓመታዊ የበጀት ጣሪያ ረቂቅ የውሣኔ ሐሳብ ያቀርባሉ/ይወስናሉ፡፡
2. የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ልማት ጽ/ቤት ከንቲባውን በማማከር ለእያንዳንዱ የበጀት ምድብ የተወሰነውን ጣሪያ ለአስፈፃሚ አካላቱ ያስታውቃሉ፡፡
3. የበጀት ጣሪያው ለበጀት ጥያቄዎች ዝግጅትና ምርምራ መሠረት ይሆናል፡፡
4. የከተማው አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤቱ የበጀት ጉድለት አይፈቀድለትም፡፡ በመሆኑም ወጪውን በእርግጠኝነት ከተሰበሰበ ገቢ መሸፈን ይኖርበታል፡፡
5. የከተማ አስተዳደር የከተማ ምክር ቤት ያልተጠበቁ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በልዩ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር በብድር እና ለተለየ ዓላማ ከተሰጠ ዕርዳታ የሚገኝ ገንዘብ የሚውለው ለተለዩ ሥራዎች ሲሆን፣ ይህንኑ ገንዘብ ለሥራ ማስኬጃ ወጪዎች መሸፈኛ እንዲውል ማዘዋወር አይቻልም፡፡ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች በመመሪያ ይወሰናል፡፡

33. Budget Ceiling and Deficit

1. The Finance and Local Economic Development Office or the municipality manager shall submit /determine draft of proposal of the city administraiton or the municipality on the basis of revenue assessment.
2. The Finance and Local Economic Development Office of the city shall, in consultation with the mayor, inform the executive body of the determined ceiling of each budget item.
3. The budget ceiling shall be a base for the preparation and examination of budget request.
4. The city administration or the municipality may not be allowed to budget deficit. Hence, it shall undoubtedly cover its expenditure from the collected revenue.
5. Unless the council of the city administration allows in special circumstances due to unexpectedly encountered economic condtions the fund made available from loan and for special purposes shall serve for special activities; it may not be possible to transfer this money to cover operational expenditures. The condition of allowing this in special circumstance shall be determined by a directive.

34. በጀት የመመርመር ሥልጣን

1. የከተማው ከንቲባ ኮሚቴ የቀረበለትን በጀት በዝርዝር መመርመር እና በምርመራው ውጤት መሠረት እንደአስፈላጊነቱ በበጀት ጥያቄው ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ እንዲደረግ ሀሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. የከተማው ከንቲባ ኮሚቴ በጀትን በመመርመር ረገድ የተሰጠው ሥልጣን በበጀት ጥያቄው ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ እንዲረግ ሀሳብ በማቅረብ ላይ የተገደበ በመሆኑ የለውጥ ወይም የማሻሻያ ሀሳቡን

34. Authority to Budget Review

1. The city mayoral committee shall review the budget submitted to it in detail, and may again submit a proposal of, as may be required, a change or amendment on the budget request in accordance with the result of the review.
2. As the authority of the city mayoral committee is limited to sumitting a recommendation with regard to budget review so as to make change or amendement, it shall send its recommendation of change or amendment, as deemed necessary, to the

www.abyssinialaw.com

እንደአግባብነቱ ለከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ይልካል፡፡ጽሕፈት ቤቱም በቀረበው ማሻሻያ ላይ አስተያየቱን ጨምሮ ለየአስፈፃሚ አካላቱ ይልካል፡፡

3. የበጀት ጥያቄውን ያቀረበው አስፈፃሚ አካል በተደረገው ለውጥ ወይም ማሻሻያ የተስማማ እንደሆነ ከንቲባ ኮሚቴ የበጀት ጥያቄውን ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
4. የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም የማሻሻያ አስተያየቱ የተላከላቸው ጽ/ቤቶች ከከተማው ከንቲባ-ኮሚቴ በቀረበላቸው የማሻሻያ ሀሳብ ላይ በሃያ ቀናት ውስጥ መልስ ያልሰጡ እንደሆነ በከንቲባ ኮሚቴ የቀረበው የማሻሻያ ሀሳብ ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡
5. የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ባቀረበው የማሻሻያ ሀሳብ ላይ በአሥር ቀናት ውስጥ አስተያየቱን ያልላከ ሲሆን፣ ማሻሻያው ተቀባይነት እንዳገኘ በመቁጠር ለከተማው ከንቲባ-ኮሚቴ ያስታውቃል፡፡ የከተማው ከንቲባ በበኩሉ የቀረበውን የለውጥ እና የማሻሻያ ሀሳብ በማካል ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
6. የከተማው ምክር ቤት በቀረበለት የበጀት ጥያቄ ላይ ማሻሻያ ያደረገ እንደሆነ የበጀት ጥያቄው በማሻሻያው መሠረት ተስተካክሎ እንዲቀርብ ምክር ቤቱ በከተማው ከንቲባ ኮሚቴ አማካኝነት አግባብ ላለው የሥራ ክፍል መልሶ ይልካል፡፡
7. የከተማው ከንቲባ-ኮሚቴ በአስር ቀናት ጊዜ ውስጥ የተስተካከለውን በጀት፣አስፈፃሚ አካላቱ ያቀረቡት አስተያየት ካለ ከዚሁ ጋር ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
8. የከተማው ምክር ቤት የተስተካከለውን በጀት እና የቀረቡ አስተያየቶችን ከመረመረ እና በበጀቱ ላይ ሕዝብ እንዲወያይበት ካደረገ በኋላ ያፀድቃል፡፡
9. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1-8 የተጠቀሱትን እንደሁኔታውና አግባብነቱ

City Finance and Local Economic Development Office. The office may incorporate its own recommendation into the amendement, send same to each executive body as well.

3. Where the executive body that submitted the budget request agrees with the change or amendement already made, the mayoral committee shall submit the budget request to the city council.
4. Where the Finance and Local Economic Development Office or those offices to which the amaendement has been sent by the mayoral committee fail to reply to it within 20 days, the proposal presented by the mayoral committee is deemed acceptable.
5. Where the city Finance and Local Economic Development Office fails to send its suggestion within ten days on the amendement proposal submitted, it shall, considering the amendement as acceptable, notify the city mayoral committee. The city mayor on his/her part shall, including the change and amendement proposal so submitted, submit to the city council.
6. Where the city council makes an amendement on the budget request submitted to it, the council may re-send it to the appropriate work unit through the mayor of the city so as to cause the correction of the budget request as per the amendement thereof.
7. The city mayoral committee shall submit the amended budget, together with the suggestion of the executive bodies, if any, to the city council within 10 days.
8. The city council shall, after going through the amended budget and submitted recommendations as well as having the budget discussed by the people, approve same.
9. Particulars under Art. 36 sub articles 1-8 hereinabove, depending on the condtion and

www.abyssinialaw.com

እየታየ የማዘጋጃ ቤቱ መሪና ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅ የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት በኩል ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

appropriateness, shall be implemented thorugh the manager of lead municipality and sub municipality, and through the woreda administrative council.

35. የሕዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ መድረክ

1. በከተማ አስተዳደሮችም ሆነ በማዘጋጃ ቤቶች በየደረጃው በሚደረግ የበጀት ምርመራ የሕዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ መድረክ ይኖራል፡፡
2. ሕዝቡ ስለበጀቱ ያለውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ፣ በሕዝብ አስተያየት መድረኮች ከሌሎች መካከል በሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡
   ሀ/ በቅደም ተከተል ሊከናወኑ የሚገባ ተግባራት፣
   ለ/ የወጪ አሸፋፈን ዘዴ፣ እና
   ሐ/ የበጀት አፈፃፀም የድርጊት መርሃ ግብር እና ሌሎች የሕዝብ አስተያየት መድረኩን በሊቀመንበርነት የሚመራው ሰው የሚያቀርባቸው ጉዳዮች፡፡

35. Public Opinion Poll

1. There shall be a public opinion poll as regards the budget review undertaken by the city administrations and municipalities at any level.
2. With the view to enhancing public awarness of the budget, at the public opinion forum, concentration shall be made on the following principal issues, among others:
   A. Activities to be accomplished in a sequence;
   B. Expenditure covering method; and
   C. Issues the person who chairs the budget execution program and other public opinion forums suggest.

36. ተጨማሪ በጀት

1. የበጀት ጥያቄ የፋይናንስ ዕቅድን ጨምሮ ከተዋሀደው ዕቅድ ጋር በተያያዘው ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ጉዳዮች የያዘ እና የተዋሀደው ዕቅድ አፈፃፀም ዕቅዱ ለተዘረጋባቸው የበጀት ዓመታት በትክክል የተከፋፈለና በተለይም በጀቱ በተጠየቀበት ዘመን ተፈፃሚ የሚሆነውን የዕቅዱን ክፍል በሚገባ ለይቶ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም በዚያው የበጀት ዓመት ውስጥ ተጨማሪ በጀት መጠየቅ አይኖርበትም፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤቱ የፖሊሲ ለውጥ በማድረጉ ወይም ሌሎች ያልተጠበቁ ጣልቃ ገብ ጉዳዮች በማጋጠማቸው ምክንያት አዲስ እና ተጨማሪ በጀት አስፈላጊ ሲሆን የስራ ክፍሉ ለከንቲባ ኮሚቴ የተጨማሪ የበጀት

36. Supplementary Budget

1. A budget requestion shall contain matters which would be incorporated in the budget estimates annexed to the harmonized plan, the fiscal plan, and the execution of the harmonized plan shall properly be classified right in the fiscal years and it shall specially indicate parts of the plan to be executed in the year of the request. As a result, no request for supplementary budget shall be made in the same budget year.
2. Without prejudice to the provision of sub-article 1 of this article, where policy change of city administration or municipality or other unforeseen intruding matters necessitate new and supplementary budget, the department may submit supplementary budget requisition to the mayoral committee. The city mayoral committee again

www.abyssinialaw.com

ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የከተማው ከንቲባ-ኮሚቴ የቀረበለትን የተጨማሪ በጀት ጥያቄ እንዲፀድቅ ከአስተያየቱ ጋር ለከተማው ምክር ቤት የማዘጋጃ ቤት እንደሆነም ስራ አስኪያጁ ለወረዳ አስተዳደር ም/ቤት ያቀርባሉ፡፡

37. የበጀት ዝውውር እና ቁጥጥር

የሀብት አጠቃቀምን ብቃት ለማረጋገጥ፣-

1. የከንቲባ ኮሚቴው ወይም የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት በአንዱ ወይም በሌላው የበጀት ምድብ ጥቅም ላይ ያልዋለ ገንዘብ መኖሩን ሲያረጋግጥ ከአንድ ጽ/ቤት ወደ ሌላ ጽ/ቤት ወይም በአንድ ማዘጋጃ ቤት ስር ከአንድ ስራ ወደሌላ ስራ የበጀት ዝውውር ሊያደርግ ይችላል፡፡ ኮሚቴው ወይም ምክር ቤቱ ውሣኔውን ከመስጠቱ በፊት የገንዘብና የአካባቢ ልማት ጽ/ቤቱን ወይም የማዘጋጃ ቤቱን ሥራ አስኪያጅ ማማከር አለበት፡፡
2. በአንድ የበጀት ምድብ ውስጥ ከካፒታል ወደ መደበኛ በጀት ዝውውር ማድረግ የሚቻለው በከተማው ከንቲባ አቅራቢነት የከንቲባ ኮሚቴው ወይም ለማዘጋጃ ቤት ከተሞች ሲሆን ደግሞ በስራ አስኪያጁ አቅራቢነት የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት ሲፈቅድ ይሆናል፡፡
3. የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም የማዘጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ በከተማው ባሉ ጽ/ቤቶች መካከል ከአንዱ ጽ/ቤት ወደሌላው በማዘጋጃ ቤት ከተማ ደግሞ ከአንዱ የስራ ክፍል ወደ ሌላው የበጀት ዝውውር እንዲደረግ መፍቀድ ይችላሉ፡፡
4. የከተማ አስተዳደር የጽሕፈት ቤት የበላይ ኃላፊዎች በየሥራ ክፍላቸው ከአንድ የበጀት ርዕስ ወደሌላ ርዕስ በጀት እንዲዘዋወር ለመፍቀድ ይችላሉ፡፡
5. የየመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች የተፈቀደውን በጀት፣ የበጀት ዝውውር እና

shall submit the requisition with recommendation to the city council for approval, and if municipalities, the manager shall submit to the woreda administration.

37. Budgetary Transfer and Control

So as to ascertain efficient resource utilization:

1. The mayoral committee or council of the woreda administration may transfer fund from one office to another, or from one activity to another within a municipality, where it is certain about the availability of unutilized money under one or other budget item. Prior to taking decision, the committee or the council shall consult the office of finance and local economic development, or manager of the council.
2. Transfer from capital to recurrent budget within the same budget item is possible on condition that the mayoral committee or the woreda administrative council, through mayor's or the manager's presentation, allows it.
3. Office of city finance and local economic development, or manager of the municipality allows budget transfer amongst offices in the city, and from one department to another in case of municipality.
4. Heads of city administration office permit budget transfer from one budget head to another within their corresponding department.
5. Heads of respective offices shall maintain the record for appropriated budget, budget transfer

www.abyssinialaw.com

ለእያንዳንዱ የበጀት ርዕስ የተደረገውን ድልድል የሚያሳይ መዝገብ ይይዛሉ፡፡

6. በከተማ አስተዳደሮች የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በማዘጋጃ ቤቶች ደግሞ የወረዳው አስተዳደር ገንዘብ ፕላን ጽ/ቤት በበጀት አፈፃፀሙ ላይ አጠቃላይ ክትትል ያደርጋሉ፡፡

38. የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት

1. በከተማ አስተዳደሮች የከተማ የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በማዘጋጃ ቤቶች ደግሞ ስራ አስኪያጁ የከተማውን የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋሉ፡፡ ማናቸውም የከተማው ሂሳብ በዚሁ ሥርዓት መሠረት ይመዘገባል፡፡
2. የማዘጋጃ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ የተለየ አሠራር እንዲከተል የሚጠይቅ ሆኖ በቢሮው ካልተፈቀደ በስተቀር የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓቱ በተቻለ መጠን በአገራዊው የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት መሠረት መዘጋጀት አለበት፡፡

39. የበጀት የጊዜ ሠሌዳ

የከተማው አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤቱ የክልሉን የበጀት የጊዜ ሠሌዳ መጠቀም አለበት፡፡

40. ለሕዝብ ስለማሣወቅ

በዚህ ደንብ አንቀጽ 36 መሠረት በከተማው ምክር ቤት ወይም በወረዳ አስተዳደር ም/ቤት የፀደቀው በጀት በቅደም ተከተል ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራትን እና የወጪ አሸፋፈኑን ዘዴ ከሚያሳይ መግለጫ ጋር በከተማው ጋዜጣ ታትሞ ሊወጣ ወይም በሌላ አመቺ የመገናኛ ዘዴ ለሕዝብ ሊገለፅ ይገባል፡፡

41. የከተማ አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤት የልማት ድርጅቶች በጀት

1. አግባብ ባለው ደንብ ወይም መመሪያ ለልማት ወይም አገልግሎት ለመስጠት

and allocation under each budget head.

6. Finance and local economic development office, and finance & plan office of woreda administration shall undertake the general follow up over the budgetary execution in town administrations and municipalities, respectively.

38. System of Accounting Structure

1. Office of the city finance and local economic development in city administrations, and the manager, in case of municipalities, shall have the system of accounting structure of the cities established.
2. Unless otherwise the accounting of the municipalities requires a special procedure and is so approved by the bureau, the system of accounting structure shall, as much as possible, be prepared subject to the national system of accounting structure.

39. Budget Calendar

The city administration or the municipality shall employ the regional budget calendar.

40. Publication

The budget approved by the city council or woreda administration, in accordance with article 36 of this regulation, shall be published together with clarification on activities to be performed sequentially and on the methods of expense coverage in the city's newspaper or other appropriate mass media.

41. Budget of Enterprises of City Administrations or Municipalities

1. Budget for enterprises that are established as independent profit making developmental or

www.abyssinialaw.com

በንግድ መልክ ራሳቸውን ችለው የተቋቋሙ የልማት ድርጅቶች በጀት የሚፀድቀው በየድርጅቶቹ በሚቋቋም ቦርድ ይሆናል፡፡ዝርዝሩ ድርጅቶቹ በሚቋቋሙበት ማቋቋሚያ ደንብ ይወሰናል፡፡

2. የልማት ድርጅቶች በጀት መሠረቱ ከልማት ከአገልግሎት እንቅስቃሴያቸው ወይም ከብድር ድጋፍና ከሌሎች ምንጮች ከሚያገኙት የተለያዩ ገቢዎች ይሆናል፡፡
3. የልማት ድርጅቶች ተራፊ ሂሳባቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙበት አግባብ ባለው ደንብ ይወሰናል፡፡

42. የካፒታል ፕሮጀክቶች

የከተማው ምክር ቤት ወይም የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት የአስተዳደሩን የካፒታል ፕሮጀክቶች ከማፅደቁ በፊት፣

1. ፕሮጀክቱ ለከተማው የሚኖረውን አጠቃላይ ጠቀሜታና አስተዋፅኦ፣
2. ፕሮጀክቱ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በሚኖሩት ዓመታት የሚያስፈልገውን ወጪ፣
3. በታክስና በዕቃና አገልግሎቶች ክፍያ ላይ የሚኖረውን አንድምታ ጨምሮ ሥራ ከጀመረ በኋላ ለፕሮጀክቱ ሥራ ማከናወኛ የሚያስፈልገውን ወጪ እና የሚገኘውን ገቢ፣ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

ክፍል 6
ስለክፍያ

43. ሥልጣን

ማናቸውንም ክፍያ መፈፀም የሚቻለው በምክር ቤቱ ወይም በወረዳ በፀደቀው የበጀት ወይም በበጀት ዓመቱ ውስጥ በተፈቀደው ተጨማሪ በጀት መሠረት ብቻ ነው፡፡

44. ግዴታ ስለመግባት

1. በከተማ አስተዳደሩ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ

service rendering entity shall be approved by the enterprises' respective boards. Details shall be determined by the establishment regulation of the organizations.

2. The basis of the budget of the enterprises shall be various revenues obtained from their developmental activities and services, or from loan, support and other resources.
3. How enterprises utilize their ending balance shall be determined by the appropriate regulation.

42. Capital Projects

Prior to its approval of the capital project of the administration, the city or the woreda administration council shall take the under described matters into account:

1. General purpose and contribution of the project to the city / town;
2. Expenses required in the years preceding the outset of operation of the project.
3. The expenditure required for the operation of the project, the income to be obtained and the implication of the project upon taxes, fees and charges after it starts operating.

PART SIX
DISBURSEMENT

43. Power

Any disbursement shall be made only in accordance with the budget approved by the council of woreda, or the supplementary budget appropriated in the fiscal year.

44. Commitment

1. No commitment shall be made against an

www.abyssinialaw.com

ወይም እርሱ በወከለው ሰው በፅሑፍ ካልተጠየቀ በስተቀር ከተፈቀደ በጀት ላይ ክፍያ ለመፈፀም ግዴታ መግባት አይቻልም፡፡

2. በከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ የማንኛውም መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ከብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሣ ሽህ/ በላይ የሆነ ወይም የማናቸውም የማዘጋጃ ቤት ከተማ የሥራ ኃላፊ ከብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሣ ሺ.ህ/ በላይ የሆነ ውል ከመፈረሙ በፊት እንደአግባብነቱ ለከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም በገንዘብና ፕላን ጽ/ቤት በኩል ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ጥያቄውን አቅርቦ የቅድሚያ ስምምነት ማግኘት አለበት::

3. እስከ ሁለት ዓመታት የሚቆዩ ውሎች እንደአግባብነቱ በከተማው የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም በወረዳ አስተዳደር ምክር ቤቱ መፅደቅ የሚኖርባቸው ሲሆን ለውሎቹ ማስፈፀሚያ የሚሆን ገንዘብ መኖሩ በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት፡፡

4. ከሁለት ዓመት ለበለጠ ጊዜ የሚቆዩ ውሎች የተዋሀደውን እቅድ መሰረት በማድረግ በከተማው ከንቲባ ወይም በወረዳ አስተዳደር ምክር መፅደቅ አለባቸው::

45. በአገልግሎቶች መካከል ስለሚደረግ የወጪ መደጋገፍ

የመግዛት አቅማቸው ደካማ የሆነ ነዋሪዎች የሚጠቀሙባቸውን አገልግሎቶች ለመደጎም የሚችሉ የመግዛት አቅም ያላቸው ነዋሪዎች የሚጠቀሙባቸው አገልግሎቶች ምርጫ እና ምርጫውን ለማድረግ የሚያስችል ዘዴ አገልግሎቱን ከሚሰጠው የሥራ ክፍል ጋር በመመካከር በከተማው ምክር ቤት ወይም በወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ይወሰናል፡፡

46. አጠቃቀም

ማናቸውም ክፍያ የሚፈፀመው በጀቱ

appropriation except on request by head of the city administration office, or by a person authorized by him in writing.

2. Head of any Office in a city administration, or head of any municipality town shall accordingly submit his request to and get prior consent of the city finance and local economic development office, of the council of the woreda administrative council through finance and plan office so as to sign a contract for above Birr 250,000 and 150,000, respectively.

3. Contracts of up to two years life shall be approved either by office of the city finance and local economic development or by the council of the woreda administration accordingly. The availability of fund for the execution of the contracts shall be ensured in advance.

5. Contracts of more than two years' life shall be approved by the city mayor or woreda council subject to the harmonized plan.

45. Interservice Expenditure Support

Selection of services that serve dwellers of high purchasing potential, and that can subsidize services serving dwellers of low purchasing potential, and method of making the selection shall be determined by the city council or the woreda administrative council in consultation with the service rendering department.

46. Utilization

Any disbursement shall be made within the budget

www.abyssinialaw.com

በተፈቀደበት የበጀት ዓመት ውስጥ እና በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለቀረቡ ዕቃዎች እና ለተሰጡ አገልግሎቶች ብቻ መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በተለይም የከተማ አገልግሎት ጽ/ቤትን የስራ ባሕርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለየ አሠራር ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የከተማው ምክር ቤት የተለዩ የራሱ ዝርዝር የተለየ መመሪያ ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል፡፡

year for goods and services rendered in same year; provided, however, that where distinctive work features of executive organs in the city administration, especially office of the city service, necessitate setting special procedure, the city council may issue its detailed directive and put into effect.

47. ወጪ ስለማድረግ

የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሐላፊ ወይም የማዘጋጃ ቤት ስራ አስኪያጅ ከበላይ ሐላፊዎች በሚሰጣቸው የፅሑፍ ሥልጣን መሠረት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ዓላማዎች የሚውል ገንዘብ ከባንክ ሂሳብ ወጪ ለማድረግ ወይም ወጪ ለማድረግ የሚያስችል ውክልና መስጠት ይችላሉ፡፡

ሀ/ በፀደቀው በጀት መሠረት የተፈቀዱ ወጪዎችን ክፍያ ለመፈፀም፣

ለ/ ምክር ቤቱ በጀቱን እስከሚያፀድቅ ድረስ መፈፀም ያለባቸውን ክፍያዎች ለመፈፀም፣

ሐ/ አግባብ ባለው የሕግ ድንጋጌዎች በተወሰነው መሠረት ያልተጠበቁ እና ሊቀሩ የማይችሉ ክፍያዎችን ለመፈፀም፣

መ/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ በሌላ ሰው ወይም የመንግሥት አካል ስም አስተዳደሩ የተቀበለውን ገንዘብ፣ የገንዘቡ ባለቤት ለሆነው ሰው ወይም የመንግሥት አካል ለመክፈል፣

ሠ/ በስምምነቱ መሠረት አስተዳደሩ በሌላ ሰው ወይም የመንግሥት አካል ስም የሰበሰበውን ገንዘብ፣

ረ/ አስተዳደሩ በሌላ ሰው ወይም የመንግሥት አካል ስም የተቀበለውን የመድን ካሣ ወይም ሌላ ማናቸውም ክፍያ፣

47. Withdrawal

Head of finance and local economic development or mayoral manager, in accordance with the authorization from heads in writing, may withdraw a sum of money from bank account, or delegate his authority to someone to do so for following purposes.

A. To incur expenditures appropriated in accordance with the approved budget;

B. To disburse expenses to be released until the council approves the budget;

C. To execute emergency and indispensable expenditures in accordance with appropriate legal provisions;

D. To disburse money the administration has received on behalf of an individual or a government organ, including under mentioned payables, to the individual or the governmental owner;

i. Money the administration has collected on behalf of an individual or a public organ on the basis of agreement;

ii. Insurance fee or any other charge the administration has received in the name of an individual or a public body.

www.abyssinialaw.com

ሰ/ በአስተዳደሩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ በስህተት ገቢ የተደረገን ገንዘብ ለመክፈል፣

ሸ/ በዋስትና ወይም በመያዣ መልክ የተቀመጠን ገንዘብ ለመክፈል፣

ቀ/ በአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት በተወሰነ ማዕቀፍ ለጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና ለኢንቬስትመንት ዓላማዎች የሚውል ገንዘብ፡፡

E. To repay money deposited in the bank account of the administration by mistake;

F. To disburse fund kept as as security and a guarantee;

G. To pay money for the purpose of cash administration and investment in a limited framework on the basis of the decision of the administration.

48. ለጥቃቅን ወጪዎች የሚውል ገንዘብ

እንደአግባብነቱ የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም የወረዳ አስተዳደር ም/ቤቱ በሚያወጡት መመሪያ መሠረት ለጥቃቅን ወጪዎች የሚውል የተወሰነ ገንዘብ በካዝና እንዲቀመጥ ለመፍቀድ እና አስተዳደሩንም ለመወሰን ይችላሉ፡፡

48. Money for Petty Cash

Office of finance and local economic development, or council of the woreda administration may accordingly permit a certain sum of money to be kept in a safe, determine its administration, too, subject to the directives the offices may issue.

49. የአጭር እና የረዥም ጊዜ የደመወዝ ብድር

እንደአግባብነቱ የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም የወረዳ አስተዳደር ም/ቤቱ በሚያወጡት መመሪያ መሠረት በአጭር እና በረዥም ጊዜ የሚመለስ የደመወዝ ብድር ለቋሚ ሠራተኞች ሊሰጥ ይችላል፡፡

49. Long and Short-Term Salary Borrowing

Office of finance and local economic development, or council of woreda administration may allow, in accordance with the directive it may issue, salary borrowing, which is to be repaid in the short and long term, to permant employees.

50. ጥቅም ላይ ያልዋለ ገንዘብ

1. ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደ እና ጥቅም ላይ ያልዋለ ገንዘብ ለአስተዳደሩ የገንዘብና የአከባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የትሬዠሪ ሂሳብ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተነገረው ቢኖርም በበጀት ዓመቱ ጥቅም ላይ ሳይውል የቀረ በዕርዳታና በብድር የተገኘ ገንዘብ በብድር እና በዕርዳታ ስምምነቱ መሠረት ጥቅም ላይ መዋሉ ይቀጥላል፡፡

50. Unutilized Money

1. The money appropriated in a fiscal year but not utilized shall be refunded to the treasury account of the finance and local economic development office of the administration.
2. Notwithstanding to the provision of sub-art. 1 of this Article hereof, money obtained in loan and aid, which is not utilized in the fiscal year, shall continue to be utilized as per the loan and aid agreement.

51. የወጪ ተመላሽ

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ተመላሽ የተደረገ የወጪ

51. Refund of Expenditure

Any refund of an expenditure in the fiscal year shall be

www.abyssinialaw.com

ሂሣብ በመጀመሪያ ወጪው፣ የቅድሚያ ክፍያው ወይም ክፍያው በተመዘገበበት ርዕስ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

52. የገቢ ተመላሽ

ለአስተዳደሩ በስህተት ገቢ የተደረገ ወይም ሕግ ከሚፈቅደው በላይ የተሰበሰበን ገንዘብ የተፈቀደ በጀት መኖሩ ሳያስፈልግ ገቢው በተመዘገበበት ርዕስ ወጪ አድርጎ መመለስ ይቻላል፡፡

ክፍል 7
ስለግዥ

53. የግዥ መርሆዎች

1. በዕቃና አገልግሎት ግዥ ተግባር ላይ የተሠማሩ የአስተዳደሩ የበላይ ሐላፊዎች እና ሠራተኞች ግዥው ለገንዘብ ተመጣጣኙን ዋጋ በሚያስገኝ አኳኋን መፈፀሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
2. የዕቃዎች አጠቃቀም ብቃት በከፍተኛ ደረጃ የሚቀንስ መሆኑ በበቂ ማስረጃ ካልተረጋገጠ በስተቀር የአነስተኛና የጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን ዕድገት ለማገዝ ከውጭ አገር ከተመረቱ ተመሳሳይ ዕቃዎች ይልቅ ለአገር ውስጥ ምርቶች ቅድሚያ መስጠት አለበት ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት በልዩ አስተያየት ለሀገር ውስጥ ምርቶች ቅድሚያ ተሰጥቶ ግዥ እንዲፈፀም ሲደረግ በአገር ውስጥ የተመረተው ዕቃ ዋጋ በውጭ አገር ለተመረቱ ዕቃዎች ከተሰጠው ዋጋ 10 የሚበልጥ መሆን የለበትም፡፡

54. የግዥ መመሪያ ስለማውጣት

ቢሮው ይህንን ደንብ መሰረት በማድረግ ለከተሞችና ለማዘጋጃ ቤቶች የሚያገለግል የግዥ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

credited to the appropriation against which the related expenditure, advance and payment was made.

52. Refunds of Revenue

It may be possible to repay money, wrongly deposited for the administration, or collected exceeding legal limit, withdrawing same form the title under which it has been registered as revenue irrespective of the availability of appropriated budget for this purpose.

PART SEVEN
PROCUREMENT

53. Principles of Procurement

1. Heads of the administration and employees who are engaged in purchasing activities of goods and services shall have the responsibility to ensure that the procurement has been executed in a manner that provides equivalent value to the money.
2. Unless it is proved with sufficient evidence that the effective use of properties is highly deteriorated, priority shall be given to domestic products rather than same goods of foreign country so as to boost the development of micro and small-scale industries.
3. Where procurement is, pursuant to the provision of sub-art.2 of this Article hereof, executed giving priority, with special recommendation, to local products, price of the local products shall not exceed of the price of foreign product by 10%.

54. Issuance Procurement Directive

The Bureau may, in accordance to this regulation, issue a procurement directive for the service of the cities and municipalities.

www.abyssinialaw.com

55. አገልግሎቶች በሦስተኛ ወገን እንዲሰጡ ስለማድረግ

የከንቲባ ኮሚቴው ወይም የወረዳ አስተዳደር ም/ቤቱ አንዳንድ አገልግሎቶች ለሦስተኛ ወገን እንዲሰጡ እና እንዲከናወኑ ማድረግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይገለፃል፡፡

55. Outsourcing Services to Third Party

The mayoral-committee or the woreda administrative council may outsource the deliberation and performance of certain services to a third party. Particulars shall be stipulated by a directive which the Bureau may issue.

ክፍል 8
የዕዳ ምህረት እና ዕዳን ከመዝገብ ስለመሰረዝ

PART EIGHT
REMISSION AND WRITE-OFFS

56. የዕዳ ምህረት

1. የከተማው ምክር ቤት በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት ከከንቲባው ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከከተማው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ከማንኛውም ግብር፣ በዚሁ ላይ ከሚከፈል ወይም ከተከፈለ ወለድም ሆነ ቅጣት ጭምር ምህረት ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. በተመሣሣይ ሁኔታ በማዘጋጃ ቤት ደረጃ የማዘጋጃ ቤቱ ሐላፊነት በሆኑ ግብሮች፣ክፍያዎችና ቀረጦች እንዲሁም ቅጣቶች ላይ ምሕረት የሚያደርገው በማዘጋጃ ቤት ምክር ቤቱ በኩል አስተያየት ተሰጥቶበት ሲቀርብ በወረዳ ምክር ቤቱ ነው፡፡
3. የከተማው ከንቲባ ኮሚቴ ወይም የማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት ከማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሳብ እና በዚሁ ላይ ከሚከፈል ወይም ከተከፈለ ወለድ ጭምር ምህረት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ምህረት የሚደረግበት ሥርዓት በከተማው ምክር ቤት ወይም በወረዳው አስተዳደር ም/ቤት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

56. Remission

1. The city council may, believing that there is a good reason and upon the recommendation submitted to it from the cities' finance and economic development office, remit any tax including any payable or paid interest thereon and penalty.
2. In a similar way, the remission of taxes, payments, dues, as well as penalties which are the responsibilities of municipality at municipal level, shall be made by the woreda council upon the recommendation of the municipal council.
3. The city mayoral committee or municipal council may, believing that there is a sound reason, remit any receivable fee, payable or paid interest on it as well. The remitting procedure shall be determined by a directive to be issued by the city council or the woreda administrative council.

www.abyssinialaw.com

57. ዕዳን ስለመሠረዝ

1. በከተማ አስተዳደር የከተማ ምክር ቤት ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ.ህ) እስከ ብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን ብር) የሆነን ተሰብሳቢ ሂሳብ ወይም መፈፀም ያለበት ግዴታ ከሂሳብ መዝገብ ሊሠርዝ የሚችል ሲሆን በከተማ አስተዳደር ከብር 1,000,00 (አንድ ሚሊዮን ብር) በላይና በማዘጋጃ ቤት ደረጃ ደግሞ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ.ህ ብር) በላይ የሆነን ተሰብሳቢ ዕዳ መሠረዝ የሚቻለው በቢሮው ውሣኔ መሰረት ይሆናል፡፡
2. በከተማ አስተዳደር የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሐላፊ በማዘጋጃ ቤት ከተማ ደግሞ ስራ አስኪያጁ ከብር 5000 (አምስት ሺ.ህ) ብር የማይበልጥን ተሰብሳቢ ሂሳብ ወይም መፈፀም ያለበትን ግዴታ ከሂሳብ መዝገብ ሊሠርዝ ይችላል፡፡
3. በከተማ አስተዳደር ከንቲባው በማዘጋጃ ቤት ደግሞ የማዘጋጃ ቤት ምክር ቤቱ ከብር 5,000 (አምስት ሺ.ህ ብር) የማያንስ እና ከብር 10,000 (አስር ሺ.ህ ብር) የማይበልጥን ተሰብሳቢ ሂሳብ ወይም መፈፀም ያለበትን ግዴታ ከሂሳብ መዝገብ ለመሠረዝ ይችላል፡፡
4. በከተማ አስተዳደር የከንቲባ ኮሚቴው በማዘጋጃ ቤቶች ደግሞ የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ከብር 10,000(አሥር ሺ.ህ) እስከ 100,000 (አንድ መቶ ሺ.ህ)የሆነን ማናቸውንም ተሰብሳቢ ሂሳብ ወይም መፈፀም ያለበትን ግዴታ ከሂሳብ መዝገብ ለመሠረዝ መወሰን ይችላል፡፡
5. በከተማ አስተዳደሮችና በማዘጋጃ ቤቶች በኩል ዕዳን ከመዝገብ ለመሠረዝ የሚቻልበትን ስርዓት ለማገዝ የሚያስችል መመሪያ ቢሮው ሊያወጣ ይችላል፡፡

ክፍል 9

57. Write-offs

1. The city council in city administration may write-off receivable fee or the obligation of amounting from birr 100,000 (one-hundred thousand) up to birr 1,000,000 (one-million) from the account record, provided, however, that the writing off receivable debt of over 1,000,000 (one-million) and 100,000 (one-hundred thousand birr) at city administration and municipal level, respectively, shall be possible by the decision of the Bureau.
2. Head of finance and local economic development office, in city administration, and the manger, in municipal level, may write-off receivable fee or payable obligation not exceeding birr 5,000 (five-thousand birr) from the account record.
3. They mayor, in city administration, and the municipal council, in a municipality, may write-off receivable fee or obligation of not less than birr 5,000 (five thousand birr) and of not exceeding birr 10,000 (ten-thousand birr) from the account record.
4. The mayoral committee in city administration and woreda administrative council in municipality may decide to write-off any receivable fee or payable obligation from Birr 10,000 (ten-thousand birr) to Birr 100,000 (one hundred thousand) from the account record.
5. The Bureau may issue a directive that helps city administration as well as municipalities in the procedure of writing off the debt from record.

PART NINE
PROPERTY

www.abyssinialaw.com

ስለ ንብረት

58. መርሆዎች

የከተማ አስተዳደርና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ንብረቶች ግዥ፣ አጠቃቀም፣ ጥገና፣ ጥበቃ እና አወጋገድ የበጀት ውስንነትን ግምት ውስጥ በማስገባት የሀብት አጠቃቀምን በጠበቀ፣ ብቃት ባለው እና ውጤታማ በሆነ መንገድ መመራቱን በሚያረጋግጥ አኳኋን መፈፀም አለበት፡፡

59. ንብረት መያዝ

በግዥ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ የተገኘ ማንኛውም ንብረት ብቸኛ ዓላማ የፀደቁ ፕሮግራሞችን አመራር እና አፈፃፀም ብቃት ባለው እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ማስቻል መሆን አለበት፡፡

60. አጠቃቀምና አጠባበቅ

እያንዳንዱ የከተማ ሆነ የማዘጋጃ ቤት አስተዳደር በይዞታው ሥር ያለው ንብረት በመልካም ሁኔታ መጠበቁን እና ምርታማ በሆነ አኳኋን ጥቅም ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

61. የጥበቃና የቁጥጥር መዝገብ

1. እያንዳንዱ የከተማም ሆነ የማዘጋጃ ቤት አስተዳደር በኃላፊነቱ ሥር ስላለው ንብረት የተሟላ መዝገብ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. እንደአግባብነቱ የከተማው የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም የማዘጋጃ ቤት ስራ አስኪያጅ ስለሚመለከታቸው የአስተዳደሩ ንብረቶች የተሟላ መዝገብ እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚያዘው መዝገብ የእያንዳንዱን ንብረት ዝርዝር የሕይወት ታሪክ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

58. Principles

The procurement, utilization, maintenance, protection and disposal of properties of city administrations and municipal cities shall be implemented in such away that ensuring efficient, effective and wise utilization of resource, as well as, taking budget limitation into accounts.

59. Holding Property

The sole objective of each property obtained in procuring or in any other way shall be to enable the management and implementation of the approved programs to be accomplished in an efficient and effective way.

60. Utilization and Protection

Each city and municipal administration is responsible for ensuring whether the property under its ownership is protected in a good condition and used in a productive manner.

61. Record Of Custody and Control

1. Each city and municipal administration is responsible for keeping complete record pertaining to the property under its authority.
2. The city finance and local economic development office or municipal manager shall, as may be appropriate, cause the maintenance of complete record pertaining to the concerned properties of the administration.
3. The record to be kept shall, pursuant to this Article, incorporate detailed history of each property.

www.abyssinialaw.com

62. የንብረት አስተዳደር

1. እንደአግባብነቱ የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወይም የማዘጋጃ ቤት ስራ አስኪያጅ በየኃላፊነታቸው አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የሕይወት ዘመን ሥርዓትን እንዲከተል ማድረግ አለባቸው፡፡
2. የከተማው ወይም የማዘጋጃ ቤት አስተዳደር በይዞታው ሥር የሚገኝ ንብረቱን ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እና የዋጋ ትመና ማካሔድ አለበት፡፡
3. ቢሮው ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር የከተሞች ንብረት ዋጋ የሚተመንበትን እና ወጪው የሚሠላበትን ዘዴ መመሪያ በማውጣት በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት እንዲሠራባቸው የተዘረጉ አሠራሮችና መመሪያዎች እስካልደረሱ ድረስ ባለው ሁኔታ ሥራ ላይ መዋል አለባቸው፡፡

62. Property Administration

1. The finance and local economic development office or municipal manager shall, as may be appropriate, make property administration under their respective authorities follow life-time-approach.
2. The city or municipal administration shall undertake annual inventory and value assessment of the property under its hold.
3. The Bureau shall, in consultation with the Regional Finance and Economic Development Bureau, cause the implementation of the methods of assessing the value of properties of cities and calculating their expenditure by issuing a directive thereof.

63. የንብረት አወጋገድ

1. በእርጅና እና በቴክኖሎጂ ለውጥ ወይም ንብረቱ ለሥራ ክፍሉ አስፈላጊ መሆኑ በመቋረጡ ምክንያት ሥራ ላይ ሊውል የማይችል ንብረት ወዲያውኑ መወገድ አለበት፡፡
2. የንብረት አወጋገድ በሚከተለው ቅደም ተከተል ይፈፀማል፡፡
   ሀ/ በአስተዳደሩ ስር ሌላ የሥራ ክፍል በማስተላለፍ፣
   ለ/ ንብረቱን የሚቀበል አካል በማይኖርበት ጊዜ በሽያጭ፣
   ሐ/ ንብረቱ በማናቸውም ምክንያት ሊሸጥ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ በሌላ አመቺ በሆነ መንገድ፣
3. ንብረት የሚወገድበት አኳኋን እና ሥርዓት ቢሮው ከክልሉ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር በሚያወጣው

63. Property Disposal

1. The property which is out of use due to depreciation and technological change or termination of necessity of the property to the department shall be disposed forthwith.
2. Disposal of the property shall be implemented in order of the following.
   A. By transferring to another department under the administration;
   B. By sale, where there is no body to receive the property;
   C. By any other appropriate way where the property can not be sold under any circumstances.
3. The system and manner of property disposal shall be determined by a directive which the Bureau may, in consultation with Regional Finance and

www.abyssinialaw.com

መመሪያ ይወሰናል፡፡

Economic Development Bureau, issue.

64. ከንብረት ሽያጭ ስለሚገኝ ገቢ

ከንብረት ሽያጭ የሚገኝ ገቢ እንደአግባብነቱ በአስተዳደሩ ዋና የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ እየተደረገ በሽያጭ የተወገደውን ንብረት ለመተካት ይውላል፡፡ ይሁን እንጂ ይኸ የመተካት አማራጭ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ አስተዳደሩ ገንዘቡን ለሌላ ተመሳሳይ ወይም አስፈላጊ ተግባር ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

64. Income From Property Sale

An income to be obtained from property sale shall, as may be appropriate, be deposited in the main Bank Account of the administration and serve to substitute the property disposed by selling. Provided, however that, where this replacing alternative is not found necessary, the administrating may cause the money to be invested for another similar or necessary purpose.

.

ክፍል 10
ሀብትን በልማት ላይ ስለማዋል

PART TEN
INVESTING RESOURCES ON DEVELOPMENT

65. ተራፊ ገንዘብን በልማት ላይ ስለማዋል

1. በከተማ አስተዳደር ተራፊ ገንዘብ በሚኖርበት ጊዜ የከተማው ከንቲባ የከተማውን ምክር ቤት በማስፈቀድ ከከተማው የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በሚያገኘው ምክር መሠረት ተራፊው ገንዘብ በተመረጡ የዋስትና ሰነዶች ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. የከተማው የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ከቦርዱ ጋር በአንድነት በመሆን ተራፊው ገንዘብ ሥራ ላይ የሚውልባቸውን የዋስትና ሰነዶች፣ የዋስትና ሰነዱን እና አክሲዮኑን ለሽያጭ የሚያውለውን ኩባንያ የፋይናንስ አቋም በማጥናት ችግር የማይፈጠር ስለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት አለባቸው፡፡
3. የከተማው ምክር ቤት የከተማው ገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በሚያቀርበው ምክር እና አስተያየት ላይ በመመሥረት ተራፊ ገንዘብ ንግድ ባልሆኑ ስራዎች ላይ በታቀዱ አገልግሎቶች ላይ እንዲውል ማድረግ ይችላል፡፡

65. Investing Surplus Money on Development

1. Where there is surplus money in the city administrations, the city mayor may, upon permission granted from the city council and on the basis of consultation from finance and local economic development office, have surplus be invested on selected securities.
2. The city finance and local economic development office together with the board shall ascertain that a problem may not be created by studying the securities whereby the surplus puts into effect, and the financial stand of the company that sells the securities and the share.
3. The city council may, based on the advice and recommendation which the city finance and local economic development office offers, cause the investement of the surplus on palnned services of non-commercial activities.

www.abyssinialaw.com

66. የጥሪት ፈንድ

የከተማ አስተዳደሩ ለረዥም ጊዜ ብድር መክፈያ እና ለቋሚ ንብረቶች መተኪያ የሚውል የጥሪት ፈንድ በህግ ማቋቋምና ማስተዳደር ይችላሉ፡፡

67. የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር

የከተማው አስተዳደሩ ወይም ማዘጋጃ ቤቱ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሚወሰነው ማዕቀፍ ክልል ውስጥ በመሆን ተገቢ የሆነ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር እና ሀብትን በልማት ላይ የማዋል ፖሊሲ ማውጣት አለበት፡፡

ክፍል 11
ሂሳብ እና የሂሳብ አመዘጋገብ

68. የሂሳብ ዝግጅትና ሪፖርት አቀራረብ

1. ማናቸውም የከተማ አስተዳደሩ ወይም የማዘጋጃ ቤቱ የሂሳብ መግለጫ ዝግጅት በጀት ከሚመደብላቸው የሥራ ክፍሎች ይጀምራል፡፡
2. የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ዕዳ እና ሀብትን እንዲሁም የተጣራ ቀሪ ሀብትን የሚያሳይ የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት፡፡ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ በሚከተሉት ሳይወሰን፣
   - ሀ/ የሂሳብ ሚዛን መግለጫ፣
   - ለ/ የገቢ እና የወጭ መግለጫ፣
   - ሐ/ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ፣ ተጨማሪ የሂሳብ መረጃዎችን የሚያካትት መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ከዚህ በላይ የተነገረውን መሠረት በማድረግ የሚመለከተው የከተማው አስፈፃሚ መስሪያ ቤት የበላይ ሐላፊ የየበጀት ዓመቱን አጠቃቀም የፋይናንስ መግለጫ በማጠቃለል ለውጭ ኦዲተር ያቀርባል፡፡
4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የተነገረውን መሠረት በማድረግ ማንኛውም የማዘጋጃ

66. Sinking Fund

The city administration may legally establish and administer a sinking fund for payment of long term loan, and for replacement of fixed assets.

67. Cash Administration

The city administration or the municipality shall, being within the framework to be decided by the Regional Finance and Economic Development Bureau, issue a policy of appropriate cash administration and investment of resources in development.

PART ELEVEN
ACCOUNT AND ACCOUNT REGISTRATION

68. Preparation of Financial Statement and Reporting

1. Preparation of any financial statement of the city administration or municipality shall commence from the departments budget is appropriated for.
2. The accounting system of city administrations and municipalities shall consist of complete information of liabilities, asset as well as equity balance resource, without being limited by:
   - A. The balance sheet;
   - B. The income statement;
   - C. The statement of cash-flow; it shall incorporate additional financial information, too.
3. Based on the details hereinabove, a concerned head of respective executive office of the city administration shall consolidate statement of finiancial utilization of each fiscal year and submit same to an external auditor.
4. On the basis of provisions stipulated under sub-art 2 herein above, any municipal manager or

www.abyssinialaw.com

ቤት ስራ አስኪያጅ ወይም የታዳጊ ከተማ የበላይ ሐላፊ የየበጀት ዓመቱን አጠቃቀም የፋይናንስ መግለጫ በማጠቃለል ለወረዳው ሒሳብ ኦዲተሮች ወይም ለክልሉ ኦዲት መስሪያ ቤት ወይም ለስራና ከተማ ልማት ቢሮ ተቆጣጣሪዎች ለምርመራና ቁጥጥር ያቀርባል፡፡

5. የከተሞችና የማዘጋጃ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የክልሉን መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ይከተላል፡፡

6. ከላይ እንደተጠቀሰው በዚህ ዓይነት የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ እና በውጭ ኦዲተር / በሚመለከተው የወረዳ/የክልሉ አካል የተመረመረው ሂሳብ ለከተማው ምክር ቤት ወይም ለማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት ይቀርባል፡፡ የከተማው ም/ቤትም ሆነ የማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት በቀረበለት የምርመራ ሂሳብ ላይ ተወያይቶ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

7. የሂሣብ ሪፖርት አግባብ ባለው አካል በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የከተማ አስተዳደሮች ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ፣ የማዘጋጃ ቤቶች ደግሞ ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሲያቀርቡ፣ የከተማ አስተዳደሮች ለስራና ከተማ ልማት ቢሮ ማዘጋጃ ቤቶች ደግሞ ለዞን ስራና ከተማ ልማት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተፈላጊ የሆኑ የገቢና የወጪ መረጃዎችን ያቀርባሉ ፡፡ ይኸው ዝርዝር የሰራና ከተማ ልማት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡ ስለሒሳብ ሪፖርቱ ይዘትና ዝርዝር ሁኔታ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. የከተማ አስተዳደሩ ወይም የማዘጋጃ ቤት አስተዳደር የሂሳብ አያያዝ በዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ እና ተገቢ ዘዴዎችን ሥራ ላይ የሚያውል

head of emerging city shall consolidate the financial statement of each fiscal year and submit to the woreda auditors, the Regional Audit Office or the inspectors of Works and Urban Development Bureau for auditing and inspection purpose.

5. The accounting system of the cities and municipalities shall be in line with the accounting system of the Regional state.

6. As stated herein above, the financial statement consolidated in such a manner, and the account audited by external auditor [the concerned woreda] regional body shall be submitted to the city or municipal council. The city council or the municipal council shall discuss on the audit report and cause corrective measure to be taken thereof.

7. The city administrations and municipalities shall, in the time decided by appropriate body, submit account report to the Regional Finance and Economic Development Bureau, and to woreda finance and economic development office, respectively; whereas city administrations and municipalities shall submit, as well, necessary income and expenditure records to the Works and Urban Development Bureau and to Zonal Works and Urban Development Branch Offices respectively. Such particular shall be determined by a directive to be issued by the Works and Urban Development Bureau. The Finance and Economic Development Bureau may issue a directive concerning the content and details of the financial report.

8. The accounting of the city administration or municipal administration shall be based on the modern accounting system, and put the appropriate methods into effect.

www.abyssinialaw.com

መሆን አለበት፡፡

69. ስለሂሳብ ሪፖርቶች መጣጣም

የከተማ አስተዳደሩ ወይም የማዘጋጃ ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ከክልሉ የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

69. Harmony of Financial Reports

Financial reporting system of city administration or municipal administration shall be harmonized with that of the Regional report.

70. ሰነዶችን ስለማቆየት

የከተማ ወይም የማዘጋጃ ቤት አስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላት ማናቸውንም የሂሳብ መረጃና መዝገብ በክልሉ መንግሥት ሕግ ለተወሰነው ዘመን ይዘው ማቆየት አለባቸው፡፡

70. Retaining Documents

The executive bodies of city or municipal administration shall retain any financial evidence and records for the period determined by the law of Regional State.

ክፍል 12
የጋራ የፋይናንስ ቦርድ

PART TWELVE
COMMON FINANCIAL BOARD

71. የጋራ የፋይናንስ ቦርድ ስለማቋቋም

1. በዚህ ደንብ የከተማ አስተዳደሮች እና የክልል መንግሥት የጋራ የፋይናንስ ቦርድ ይቋቋማል፡፡ የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፡፡
2. የጋራ የፋይናንስ ቦርድ በክልሉ ውስጥ ካሉ ከተሞች አስተዳደሮች እና ከክልሉ መንግሥት የተወከሉ አባላት ይኖሩታል፡፡ የየከተሞቹ የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሐላፊዎች በየተራ እየተወከሉ እና የክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ የቦርዱን ሊቀመንበርነት በየተራ ይይዛሉ ወይም በሁለቱ በጋራ የሚመደብ ሰው ቦርዱን ይመራል፡፡ ሆኖም አጀንዳው የተለየ አትኩሮት የሚጠይቅ በሚሆንበት ጊዜ ስብሰባው በጋራ ሊመራ ይችላል፡፡
3. በጋራ የሚመራው አጀንዳ አግባብ ባለው የፋይናንስ ኃላፊ ምክር ላይ ተመስርቶ እንደአግባብነቱ በክልሉ የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ሐላፊ ወይም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

71. Establishing of Common Financial Board

1. Common financial board of the city administrations and the Regional state shall be established by this regulation. The board shall be accountable to the Regional Government Council.
2. The common financial board shall constitute members representing city administrations in the region and the Regional Government. The heads of the finance and local economic development office of each city, being delegated turn by turn, and the Regional Finance and Economic Development Bureau head shall hold chairpersonship in turn or a person to be assigned by both parties jointly shall direct the board; provided, however that, where the agenda requires special attention, the meeting may be presided over jointly.
3. The agenda which is presided over in common shall, based upon advise of appropriate finance head, be determined, as may be appropriate, by the Regional Trade Industry and Urban Development or the Finance and Economic Development Bureau head.

www.abyssinialaw.com

ኃላፊ ይወሰናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በየተራ የሊቀመንበርነቱን ቦታ መያዝ አስቸጋሪ ወይም በቀላሉ ሥራ ላይ ሊውል የማይችል ሆኖ ሲገኝ የክልሉ መንግሥት ወይም የየከተማው አስተዳደር ምክር ቤቶች ለቋሚ ኮሚቴዎቻቸው ቦርዱን በቋሚነት የሚመራ ገለልተኛ ሊቀመንበር በጋራ እንዲሰይሙ መመሪያ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
5. ማናቸውም የጋራ የፋይናንስ ቦርድ ውሣኔ በሙሉ ድምፅ መደገፍ አለበት፡፡ በማናቸውም ምክንያት ውሣኔው በሙሉ ድምፅ ያልተደገፈ ሲሆን የክልሉ መንግሥት እና የከተማ አስተዳደሮች ከንቲባ-ኮሚቴዎች ቋሚ ኮሚቴዎች በጋራ ስብሰባ የቀረበውን ሀሳብ ይመረምራሉ፡፡ የቋሚ ኮሚቴዎቹ የጋራ ስብሰባ ውሣኔውን ከበከሉ አስተያየት ጋር ወደ ቦርዱ ይመልሰዋል፡፡ በዚህ ዓይነት የተፈጠረው ችግር የማይፈታ በሚሆንበት ጊዜ በቦርዱ አብዛኛው አባላት ወይም እኩል ሲሆኑ ደግሞ በሊቀመንበሩ የተደገፈው ሀሳብ የቦርዱ የመጨረሻ ውሣኔ ይሆናል፡፡
6. የቦርዱ ሊቀመንበር ለውሣኔ አሰጣጥ የሚረዳ አስተያየት የሚያቀርብ የባለሙያዎች የቴክኒክ ቡድን ይሰይማል፡፡

4. Where it is found difficult or may not be easily applicable to hold the chairpersonship turn by turn, pursuant to sub-art. 2 of this article, the Regional State or councils of the city administration may provide a direction to their standing committee to commonly assign a neutral chairperson who permanently leads the board.
5. Any decision of the common financial board shall be supported (voted) by all voices. Where the decision is not supported (voted) by all voices, on any grounds, the Regional state and the standing committees of the city administrative mayoral committees shall examine the recommendation so submitted having a joint meeting. The joint meeting of the standing committees, on its part, shall return its decision to the board with its own recommendation. Where the problem created in such a way is not solved, the idea supported by majority and, in case to tie, the side for which the chairperson has voted shall be the final decision of the board.
6. The chairperson of the board shall designate a technical team of experts who submit recommendation capable of helping the decision provisions.

72. የጋራ የፋይናንስ ቦርድ ተግባራት

1. በክልሉ መንግሥት እና በከተማ አስተዳደሮች በወረዳ አስተዳደሮችና በማዘጋጃ ቤቶችና በታዳጊ ከተሞች መካከል የሚኖረውን የፋይናንስ ግንኙነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን ያጠናል፣ ይመረምራል፣ የውሣኔ አስተያየት ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፤ የክልሉን መንግስት በነዚህ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፡፡
2. ከዚህ በላይ በተነገረው ሳይወሰን ቦርዱ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡

72. Duties of Common Financial Board

1. Studies, examines issues concerning financial relations to be established between the Regional State and city administrations, woreda administrations and municipalities as well as emerging cities, submits recommendations to the Regional State, and advises the Regional state on these issues.
2. Without being limited only the stipulated hereinabove, the board shall focus on the following affairs.

www.abyssinialaw.com

ሀ/ የገቢ ክፍፍል

1. የመነሻ ግምትን መሠረት በማድረግ የከተማ አስተዳደሮች ክልሉ ከሚሰበሰበው ገቢ ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ እያጠና አስተያየት ያቀርባል፡፡
2. የገቢ ክፍፍል ዘዴዎችን ያዘጋጃል፣ በዘዴዎቹ ውስጥ ታሳቢ የሚሆኑ መመዘኛዎችን ያካትታል፡፡ መመዘኛዎቹን በሚያዘጋጅበት ጊዜ ታሳቢ ያደረጋቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

ለ/ ዕርዳታ እና ድጋፍ

1. ቦርዱ ከክልሉ መንግሥት ለከተሞች እና ከወረዳ አስተዳደሮች ለማዘጋጃ ቤቶች ለታዳጊ ከተሞች የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ ዓይነትና መጠን ወስኖ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እንዲመከርበትና እንዲወሰንበት ያቀርባል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተነገረውን ሥራ ላይ ለማዋል ቦርዱ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡
   - ሀ/ ለከተማ አስተዳደሮች የሚሰጠውን ድጋፍ ዕቅድና አሸፋፈን ሁኔታ ይመረምራል፣
   - ለ/ የከተሞችን የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ አቅጣጫ ስትራቴጂና ትኩረት ይመረምራል፡፡
   - ሐ/ ጠቅላላው ዕርዳታ በዕርዳታ ተቀባይ የከተማ አስተዳደሮች መካከል የሚከፋፈልበትን ዘዴ አስተያየት ያቀርባል ፡፡
   - መ/በወረዳ አስተዳደሮችና በማዘጋጃ ቤቶችና ታዳጊ

A. Revenue Sharing

1. Based upon the initial assessment, studies the share city administrations may have from the revenue collected by the region, and submit recommendation thereof.
2. Prepares methods of revenue-sharing, incorporates standards considered within the methods. It shall apparently put principal affairs it has considered where preparing the standard.

B. Aid and Assistance

1. The board shall, determing the type and amount of financial support to be made available from the regional government to cities, and from the worked administrations to municipalities and emerging cities, submit to the Regional Government Council for deliberation and decision thereof.
2. In order to apply the provision stipulated under sub-art 1 hereinabove, the board shall perform the following activities:
   - A. Examine the plan of assistance to be rendered to city administrations, and the coverage conditions;
   - B. Examine the strategy, focus and direction of development and service delivery of cities;
   - C. Submit recommendation pertaining to the method as to how the total aid may be distributed amongst aid receiving city administrations;
   - D. Design and submit the principles, working procedures and systems

www.abyssinialaw.com

ከተሞች መካከል የሚኖረውን የበጀት ክፍፍል ድጋፍና ድርሻ የሚታመንበትንና የሚከፋፈልበትን መርሕ አሠራርና ስልት ነድፎ ያቀርባል፡፡

3. የመነሻውን ግምት መሠረት በማድረግ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር በክልሉ መንግሥት ከተገኘው ዕርዳታ ሊያገኝ የሚገባውን ድርሻ ይወስናል፡፡
4. ከክልሉ በጥቅል ለከተሞች የሚተላለፈው ገንዘብ በክልሉ ውስጥ ባሉ የከተማ አስተዳደሮች መካከል የሚከፋፈልበትን ዘዴ ይወስናል፡፡
5. ልዩ ዕርዳታ የተጠየቀለትን ወይም ይሰጠዋል ተብሎ የተወነለትን ፕሮጀክት አዋጭነት መርምሮ አስተያየት ያቀርባል፡፡

ሐ/ ብድር

1. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የብድር ጥያቄ ሲቀርብ ቦርዱ የብድሩን መጠንና ዓይነት፣ በብድሩ ገንዘብ ወጪው እንዲሸፈን የቀረበውን ፕሮጀክት ተመራጭነት አስጠንቶ አስተያየት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ብድር እንዲፈቀድ አስተያየት በሚያዘጋጅበት ጊዜ ቦርዱ፣
   ሀ/ ብድር የጠየቀውን የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አቋም በዝርዝር ያጠናል፡፡
   ለ/ የከተማውን ኢኮኖሚ እና ዕዳው በሚከፈልበት ጊዜ ለዕዳው የሚውል ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችል አስተማማኝ አቅም ያለው መሆኑን በማጥናት የከተማው አስተዳደር ዕዳ

whereby the budget sharing, support and share may be assessed and shared amongst woreda administrations, municipalities and emerging cities.

3. Determine the share which each city administration may obtain from the aid may available from the Regional State, depending on initial assessment.
4. Determine the method whereby the finance that is transferred to cities from the region in gross is shared among the city administrations in the region.
5. Examine the feasibility of the project for which special aid has been requested or determined to be rendered, and submit recommendation thereof.

C. Loan

1. Where loan request is submitted to it, the board may, if found necessary, submit the recommendation having the loan amount and type, preference of the project so presented for the coverage of its cost by the loan studied.
2. Where the recommendation is prepared to permit loan, the board shall:
   A. Study, in detail, the financial stand of the city administration which has requested loan;
   B. Study whether the city administration has a capacity to pay debt by studying the city's economy and that it has a reliable capacity which enables to collect revenue for the repay of the debt during its payment.

www.abyssinialaw.com

የመክፈል አቅም ያለው መሆኑን ያጠናል፡፡

ሐ/ በፕሮጀክት ትንተና ላይ በመመሥረት ብድር የተጠየቀለት ፕሮጀክት አዋጪ እና ዘላቂነት ያለው መሆኑን፣ አዲስ የልማት ዕቅድ እና ስትራቴጂካዊ ሚና ያለው መሆኑን እንዲሁም ለከተማው ገቢ የሚኖረውን አስተዋፅኦ ያረጋግጣል፡፡

መ/ አግባብ ባለው አካል ለበጀት ዓመቱ የተወሰነውን የብድር ጣሪያ መጠበቅ መቻሉን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ያረጋግጣል፡፡

C. Ascertain whether the project for which the loan is requested is feasible and sustainable; if it has new development plan and strategic role, as well as its contribution to the revenue of the city, based upon the project analysis.

D. Ascertain in consultation with concerned bodies whether the loan ceiling determined by the appropriate body for the fiscal year is kept.

ክፍል 13
ልዩ ልዩ

73. የገንዘብና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የከተማው ገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የከተማው አስተዳደር ዋና የሂሳብ ሹም ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህ ኃላፊነቱ በሌላ አዋጅና ደንብ የተሰጡት ተግባርና ሐላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የከተማ አስተዳደሩን በጀት አፈፃፀም ይከታተላል፡፡
2. ከከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አቋም ጋር የተያያዙ መረጃዎች በማናቸውም ጊዜ እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡
3. የሁሉንም የበጀት ዓይነቶች ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ ትክክለኛ መዝገብ ይይዛል፡፡ የከተሞች አስተዳደር የፋይናንስ መረጃ ክምችት እንዲኖር ለማድረግ የያዘውን

PART THIRTEEN
MISCELLANEOUS

73. Duties and Responsibilities of the Finance and Local Economic Development Office

The city finance and local economic development office shall serve as a chief accountant of the city administration. In such responsibility of its, without prejudice to its duties and responsibilities vested in it by other proclamation and regulation, it shall have the following duties and responsibilities.

1. follow up the budget execution of the city administration.
2. cause the availability of information related to the financial stand of the city administration at any time.
3. Maintain accurate records of expenditures and revenue of every budgetary item. Consolidate the finacncial information kept so as to make the city administrations have collection of information.

www.abyssinialaw.com

መረጃ ያጠቃልላል፡፡

4. የከተማውን አስተዳደር የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለከተማው ከንቲባ ያቀርባል፣ በግልባጩም የክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡
5. የብድር ወጪ አሸፋፈንን ይቆጣጠራል፣ የዕዳው ሚዛን በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አቅም ውስጥ መሆኑን እና የዕዳው ክምችት በአገሪቱ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት ላይ ችግር የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
6. ከንቲባው በውጭ ኦዲተሮች የተከናወነው የከተማ አስተዳደሩ የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት ለከተማው ምክር ቤት እንዲተላለፍ ለአፈ-ጉባኤው ያቀርባል፡፡
7. ማናቸውንም ሂሳብ የሚመለከት መዝገብ እና የሂሳብ መግለጫ ለአጠቃቀም በሚያመች መንገድ ይይዛል፣እንዲያዝም ያደርጋል፡፡ አግባብ ያላቸው ክፍሎች በጠየቁ ጊዜ ሊጠቀሙበት እንዲችሉ ያደርጋል፡፡

4. Prepare and submit the city administration's consolidated fund report to the city-mayor, and cause the notification of the Regional Finance and Economic Development Bureau.
5. Supervise coverage of loan expenditure; ascertain that the debt balance is within the financial capacity of the city administration, and the accumulation of the debt does not entail any problem in the macro-economic stability of the country.
6. The mayor shall submit the audit report of the city administration accomplished by external auditors to the city council.
7. Keep and cause to be kept any financial record and financial statement in a manner which is suitable for utilization; make ift accessible for concerned bodies to utilize it.

74. የክልሉ የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተግባር

በዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች ሥር የሰፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ፋይናንስ እና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣

ሀ/ በከተማ አስተዳደሮች እና በማዘጋጃ ቤቶች መልካም የበጀት እና የፋይናንስ አስተዳደር እንዲኖር ዕገዛ ያደርጋል፡፡

ለ/ የከተማ አስተዳደሮች ማዘጋጃ ቤቶች እና የከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች በዚህ ደንብ እና አግባብ ባለው በአጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት እና አንድ ወጥ በሆነ የገቢ እና የወጪ አመዳደብ ሥርዓት መሠረት ሥራቸውን የሚያከናወኑ መሆኑን ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡

74. Duties of the Regional Finance and Economic Development Bureau

Without prejudice to the particulars stipulated under other provisions of this regulation, the Regional Finance and Economic Development Bureau shall:

A. Assist the presence of good budget and financial administration in city administrations and municipalities.

B. Follow-up and evaluate whether city administration, municipalities and developmental enterprises perform their duty pursuant to this regulation and relevant and generally accepted accounting system as well as uniform revenue and expenditure allocating system.

www.abyssinialaw.com

75. የማዘጋጃ ቤቶች እና የታዳጊ ከተሞች የፋይናንስ ስርዓት

1. ማዘጋጃ ቤቶች እና ታዳጊ ከተሞች ደረጃ በደረጃ የፋይናንስ እንቅስቃሴያቸውን በዚህ ደንብ በተደነገገው የበጀት ሥርዓት የሂሳብ አያያዝ እና የሂሳብ ሪፖርት ሥርዓት መሠረት ማከናወን አለባቸው፡፡ለዚህም የሚያበቃ ስርዓትና አቅም ደረጃ በደረጃ መገንባት አለባቸው፡፡
2. የማዘጋጃ ቤቶች ዓመታዊ በጀታቸውና ዕቅዳቸው የሚፀድቀው በወረዳው ምክር ቤት ሲሆን የታዳጊ ከተሞች በጀት በተቋቋሙበት የቀበሌ ምክር ቤት ይፀድቃል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 ስለታዳጊ ከተሞች የተጠቀሰው ቢኖርም የወረዳ አስተዳደሮች የታዳጊ ከተሞችን የገቢና የወጪ በጀት በበላይነት መቆጣጠር ይችላሉ፡፡

76. ኦዲት

1. የከተማው ምክር ቤት የከተማ አስተዳደሩን ሒሳብና በጀት የሚመረምር እና የምርመራውን ውጤት ለምክር ቤቱ የሚያቀርብ በውድድር ከተመረጡ የግል ኦዲት ተቋም የውጭ ኦዲተር ይሰይማል፡፡
2. የኦዲት ሪፖርቱ ከዚህ በላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ያለፈውን የበጀት ዓመት የሂሳብ ምርመራ ግኝት እና በግኝቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ የሚያካትት መሆን አለበት፡፡
3. የከተማ አስተዳደሩ ሒሳብ በዓመቱ ተመርምሮ ሪፖርቱ ለምክር ቤቱ መቅረብ ይገባዋል፡፡ በምንም ዓይነት ሁኔታ የከተማ አስተዳደሩ ሒሳብ ሳይመረመር ከሁለት የበጀት ዓመታት በላይ መቆየት የለበትም፡፡
4. የከተማው ከንቲባ የአስተዳደሩ አስፈፃሚ

75. Financial System of Municipalities and Emerging Cities

1. Municipalities and emerging cities shall, step by step, perform their financial activities pursuant to the budgetary system, accounting, and financial reporting system stipulated in this regulation. To this end they shall gradually establishes a system and a capacity enabling to do same as well.
2. The annual budget and plan of municipalities shall be appropriated by the woreda council while that of emerging cities shall be appropriated by the kebele council in which it is established.
3. Notwithstanding the provision about emerging cities under sub-art 2 of this article hereof, the woreda administrations may supervise over the revenue and expenditure budget of the emerging cities.

76. Audit

1. The city council shall assign an external auditor selected on competitive basis among private audit institutes with the view to auditing budget and finance of the city administration and submitting the finding of the audit.
2. The audit report shall, in addition to the provisions stated above, incorporate the out-come of the audit account of the previous fiscal year and the measures taken on the finding.
3. The account of the city administration shall be audited and reported to the council within the year. The account of the city administration shall not, in any case, stay without being audited over two fiscal years.
4. The city mayor shall establish internal audit

www.abyssinialaw.com

አካላትን በጀት ብቃት ባለው ሁኔታ መጠቀም የሚያስችልና ጠካንራ የውስጥ ቁጥጥርና የሂሳብ አያያዝ ስርዓት እንዲኖር እገዛ የሚያደርግ የውስጥ ኦዲት ያቋቁማል፡፡

5. ተጠሪነታቸው ለወረዳ የሆኑ የመሪና ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶች እንዲሁም ታዳጊ ከተሞች ሒሳብ የሚመረመረው በማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት በሚሰየም የውጪ ኦዲተር ሲሆን የምርመራ ውጤቱም በአፈ-ጉባኤው በኩል ለምክር ቤቱና ለወረዳ አስተዳደር ይቀርባል፡፡

6. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 5 የተጠቀሰው ቢኖርም የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የማዘጋጃ ቤቶችና ታዳጊ ከተሞችን ሒሳብ መርምሮ ውጤቱን ለማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት አፈ-ጉባኤና ለወረዳ አስተዳደሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

7. ከዚህ በላይ ሰለማዘጋጃ ቤቶችና ታዳጊ ከተሞች የተጠቀሰው ቢኖርም የክልሉ ጠቅላይ ኦዲት መስሪያ ቤት አሰፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የከተማ አስተዳደር፣ ማዘጋጃ ቤቶችንና የታዳጊ ከተሞችን ሒሳብ ለመመርመር ይችላል፡፡

8. በዉጪ ኦዲተሮች በወረዳው ገንዘብ ኢኮኖሚ ልማትም ሆነ በአጠቃላይ ኦዲት መስሪያ ቤት በተመረመረው የሒሳበ ሪፖርት ላይ የማዘጋጃ ቤት ም/ቤቱና የወረዳ አስተዳደሩ የእርምት ርምጃ እንዲወስድ ያደርጋሉ፡፡

77. የልማት ድርጅቶች

በከተማ አስተዳደር ወይም በማዘጋጃ ቤት ሥር የሚደራጁ የልማት ድርጅቶች የሚቋቋሙበት፣ የፋይናንስ እንቅስቃሴያቸውን የሚያከናውኑበት እና የሚፈርሱበት ሥርዓት ድርጅቶቹ በሚቋቋምበት ደንብ ይወሰናል፡፡የልማት ድርጅቶች የሚቋቋሙበትን ደንብ የክልሉ ንግድ ኢንዱስትሪ ከተማ ልማት ቢሮ ሊያወጣ

enabling efficient utilization of budget of the executive bodies of the administration, and boosting the coming into existence of strong internal control and accounting system thereof.

5. The account of lead and sub-municipalities which are accountable to woreda as well as that of emerging cities shall be audited by an external auditor to be designated by municipal council, and the finding of audit shall be submitted to the council and woreda administration through the speaker.

6. Notwithstanding the provisions stated under herein above of sub-art 5, the woreda finance and economic development office may audit the account of the municipalities and emerging cities and submit the findings to the speaker of municipal council and to the woreda administration.

7. Notwithstanding the provisions stated hereinabove pertaining to municipalities and emerging cities, the Regional General Audit Office may, where it finds same necessary, audit the account of city administrations, municipalities and emerging cities.

8. The municipal council and the woreda administration cause a corrective measure to be taken on the audit report gone through by the external auditors, the woreda finance economic development office, or Office of the General Audit.

77. Development Enterprises

Procedure for establishment, financial transaction and dissolution of the development enterprises to be organized under city administrations or municipalities shall be determined by their establishing regulation. The Regional Trade, Industry and Urban Development Bureau may issue the establishing directive of the enterprises.

www.abyssinialaw.com

ይችላል፡፡

78. የሕዝብ ማስታወቂያ

የከተማው ወይም የማዘጋጃ ቤቱ ምክር ቤት በከንቲባው ወይም በማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ የሚቀርብለትን አስተያየት መሠረት በማድረግ በአስተዳደሩ ሥር የሚካተቱትን አስፈላጊ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ዓይነት የሚገልጽ የሕዝብ ማስታቂያ በከተማው ጋዜጣ ወይም በሌላ አመቺ በሆኑ የሕዝብ መገናኛ ለከተማ ሕዝብ እንዲገለፅ ያደርጋል፡፡

79. ጥፋቶችና ቅጣቶች

በከተማ ወይም በማዘጋጃ ቤት ወይም በታዳጊ ከተማ አስተዳደር ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ለማስተዳደርና ወይም ክፍያ ለመፈፀም በማናቸውም መስሪያ ቤት የተመደበ ሠራተኛ ወይም ሐላፊ ወይም ተሚ በስራው ላይ ለሚያደርሰው ጥፋት በክልሉ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 አንቀጽ 60 ስለጥፋቶቹና ቅጣቶቹ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

80. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

በዚህ ደንብ በግልፅ ተለይተው ከተሰጡት ውጪ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስችሉ መመሪያዎችን የክልሉ ስራና ከተማ ልማት ቢሮ ሊያወጣ ይችላል፡፡

81. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ጉዳዮች ደረጃ በደረጃ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ጉዳዩች ወጥተው እስካልተተኩ ድረስ እስካሁን ሲሰራባቸው የቆዩ ደንቦችና መመሪያዎች እንደፀኑ ሲሠራባቸው ይቆያሉ፡፡

82. ደንቡ የሚፀናበት ቀን

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ

78. Public Notice

The city or municipal council shall, based on the recommendation submitted to him by the mayor or the municipal manager, cause the publication of the necessary financial transactions referring the administration in the city newspaper or any other favorable mass media.

79. Offences and Penalties

Conditions specified pertaining to the offences and penalties under article 60, sub-arts 1-6 of the Regional States' Financial Administrative Proclamation No. 18/1997 shall apply to an employee or a head or a public official assigned to any office by a city or a municipality or an emerging city to collect, administer money and/or execute payment thereof upon committing offences on his duties.

80. Power to Issue Directive

The Regional Works and Urban Development Bureau may issue directives enabling the execution of this regulation, except those apparently stated in this regulation.

81. Transitory Provision

Unless procedures that enable, step by step, to emplement of matters indicated in this regulation are issued and substitute former, the existing regulations and directives that have been functional so far shall stay in force.

82. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of

www.abyssinialaw.com

ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር
መስከረም 4 ቀን 1998 ዓ.ም.
ዮሴፍ ረታ
አማራ ብሔራዊ ክልል
መስተዳድር ምክር ቤት

its publication in the Zikre Hig Gazetta of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 14th day of September, 2005
Yosef Reta
Head of Government of the Amhara
National Regional State